# የሙሽራ አመራረጥ

ብዙ የታመሙ ሰዎች አሉ። ሁሉምን በአንድ ጊዜ መድረስ አልችልም። ነገር ግን፡ አዳምጡ።

2 ዛሬ ማታ በዚህ ውብ አዳራሽ፡ በነዚህ ድንቅ ሰዎች ስብሰብ መካከል፡ እንደገና እዚህ፡ በመገኘቴ በጣም ደስተኛ ነኝ። ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት፡ ወደ ውስጥ እየገባን፡ በመንገድ ላይ የቆሙት ሰዎች፡ ወደ ውስጥ መግባት እንዳልቻሉ ነገሩኝ። እኔም፡ "መልካም፡ ምናልባት አንድ ክፍል ላገኝላችሁ እችላለሁ" አልኳቸው። እንድገቡ አልፈቀዱላቸውም ነበር። ስለዚህ ለእነሱ በቂ ቦታ ስለሌለን አዝናለሁ። የህንጻው ታችኛው ክፍልም፡ ሞልቷል ብለዋል። ስለዚህም ለዛ እናዝናለን። ነገር ግን እዚህ በመገኘታችን ደስተኞች ነን፡ እነዚህንም ሁሉ ጥሩ አገልጋዮችን፡ ነጋዴዎችን፡ ከተለያዩ ከአገሪቱ ክፍሎች የመጣችሁ ልዑካን በሙሉ በማየታችን ደስተኞች ነን።

3 ዛሬ ጠዋት በቁርስ ሰዓት ላይ የምሰበክበት ትልቅ እድል አግኝቼ ነበር፡ በእርግጠኝነት በእንደዚህ ዓይነት ጥሩ ሰዎች ፊት መሰበክ ክብር ነው ብዬ አሰባለሁ። **እንክርዳድ ከስንዴው ጋር አይወርሰም** በሚል ርዕሰ ነበር የተናገርኩት። ስብከቴን አልጨረስኩትም። ይህ ግን—የወንድማችን ስህተት አይደለም። አስተዳደሩ ትንሽ እንድንቆይ ለማድረግ ቢሞክርም፡ አልቻለም። ወንድም ዴሞስ፡ ስለዚያ በእውነት አመሰግናለሁ። ያ በጣም፡ በጣም ጥሩ ነው። እያንዳንዳችሁ፡ ላሳያችሁት ደግነት አመሰግናችኋለው። እንድንቀጥል አልፈቀዱልንም። ሰ—ስለዚህ ፕሮግራሙን መዝጋት ነበረብን። **እንክርዳድ ከስንዴው ጋር አይወርሰም** የሚለውን፡ ያንን ለመጨረስ፡ ሌላ ጊዜ፡ እቀጥላለሁ። እዚህ የነበራችሁ፡ ተረድታችሁታል? ሃሳቡን ለመረዳት የተናገርነው ነገር በቂ ነው ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።

4 አሁን፡ ዛሬ ማታ፡ የፓናል ውይይትም፡ እንዳለ አውቃለሁ፡ ስለዚህ ያ እንዳያመልጣችሁ፡ እዚህ ላቆያችሁ አልፈልግም። ምክንያቱም፡ ባለፈው ምሽት ያየነው የ—የፓናል ውይይት ለጴንጤቆስጤ-እምነት ተከታዮች፡ በእርግጥ ጠቃሚ ነበር ብዬ አሰባለሁ። እንዲህ ያሉ ጥሩ የሰዎች ሰብሰብ፡ ቀጥተኛ የሆኑ፡ ድንቅ መልሶች ነበሩ። ያንን በማየቴ፡ ጥሩ ስሜት ነው የተሰማኝ። ዛሬ ማታ፡ ጌታ እንደሚባርከው አምናለሁ። የሚያየው ሁሉ፡ ይመነው። ይህ ልባዊ ጸሎቴ ነው።

5 በዛሬው ዕለት በደብዳቤ፡ እና በስልክ፡ የሚመጡ በርካታ ሪፖርቶች እንደሚያመለክቱት፡ በዚህ ሰብሰባ ላይ ብዙ ሰዎች ተፈውሰዋል። በዚህ በጣም ተደስቻለሁ። የታመሙ፡ ሰዎችን፡ ሳይ፡ የአገልግሎቴ አይነት ያ ነውና።

6 ወደዚህ የ—የመጣሁት ለመሰበክ ነው። ታውቃላችሁ፡ እኔ ሰባኪ፡ አይደለሁም። ነገር ግን፡ በዚህ፡ በእኔ ሰዋሰው፡ "ሂዝ፡ ሃይንት" እና—እነዚያ ቃላቶች፡ ስለዚህ በ—በዛሬው ጊዜ ዘመናዊ ሰባኪ ብለን እንደምንጠራው መናገር አልችልም። እኔ ያንን መሆን አ—አልችልም፡ ምክንያቱም አ—አልተማርኩም።

7 ነገር ግን ለሌሎች ሰዎች፡ የማውቀውን፡ ወይም እንደማውቀው የሚሰማኝ፡ እንዴት እንደ ተማርኩት፡ ለሌሎች፡ መግለጽ እወዳለሁ። እሱ ሕይወቴ ሁሉ፡ ሁሌም መሆን የምፈልገው ነገር እርሱ ነው፡ ገና ልጅ ሳለሁ፡ ያውም እኔ ከማሰበው በላይ፡ በምድር ላይ፡ ጋደኛ፡ በጭራሽ አላገኝም ብዬ ባሰብኩት ዘመን ላይ ነበር። በእርግጥ ስለዛሬ ድንቅ ድንቅ ጓደኞቼ አመሰግናለሁ።

8 እኔ... [ አንድ ወንድም እንዲህ አለ፡ “ወንድም ብራንሃም፡ ከኋላ ትንሽ አይሰማም። ቀረብ በል።”—እርታዒ።] ኦህ፡ ይቅርታ። እዚህ የ—የሆነ ቦታ፡ ከትኩረት፡ ወጥቼ ነው።

9 አሁን፡ በቀጥታ ወደ አገልግሎት ለመግባት፡ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን እንመልከት። ሁል ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ እ—እወዳለሁ፡ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቃል ስለሆነ። ያንን አምናለሁ። የማይሳሳት የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ አምናለሁ። አሁን እዚህ የተጻፋ ጥቂት ጥቅሶች እና ለመጥቀስ የያዝኳቸው ጽሁፎች አሉኝ፡ ለቀጣይ ለጥቂት ጊዜያት፡ ምናልባትም ለአርባ-አምስት ደቂቃዎች፡ መመልከት እፈልጋለው።

10 ከዚያም ይህን አስደናቂ ፓናል ውይይት ዛሬ ማታ እንደገና ለማየት በጊዜ እንወጣለን። እግዚአብሔርም በቀጣይነት እንደሚባርካችሁ አምናለሁ። ምን ማድረግ እንዳለባችሁም አውቃለሁ። ዛሬ ማታ፡ ገና፡ ወደ ቱክሰን መንዳት አለብኝ፡ እያችሁ፡ መገመት ትችላላችሁ። የአሥር-ሰዓት መንገድ ነው።

11 ወደ ውጭ አገር ስለምሄድ፡ በጥዋት በመንግሥት ህክምና ተቋም ውስጥ የቢጫ ወባ ክትባት መውሰድ አለብኝ። ስ—ስለዚህ ወደዚያ መሄድ አለብኝ። በቀደም እለት፡ ለሌላ ጊዜ አስተላልፌው ነበር፡ አሁንም በድጋሜ “አይሆንም” ብላቸው እሺ አይሉም። ተጨማሪ የቴታነስ ታይፈስ እና የቡስተር ክትባት፡ መውሰድ ይጠበቅብኛል።

12 ስለዚህ፡ ስለ እድሉ፡ በጣም አመሰግናለሁ፡ ከ—ከስብሰባው በፊት ስላደረግነው ጥሩ ስብሰባም እንዲሁ። በእርግጥ ልቤን አስደስቶታል። እናንተ ጥሩ ሰዎች ናችሁ። እግዚአብሔር እንደሚባርካችሁ አምናለሁ።

13 ያ... ታላቁ አውሬ እዚያው ተጋድሞ፡ ከጥቂት ቀናት በፊት፡ በአላስካ ውስጥ ራሱን አንቀሳቅሷል፡ ዛሬ ጠዋትም እንደገና፡ ጅራቱን በዋሽንግተን፡ ዙሪያ ጥሏል። ወደዚህ አቅጣጫም፡ በቀላሉ ሊመጣ ይችል ነበር። መንፈስ ቅዱስ የሚነግረኝ ከሆነ...

14 አንድ ሰው እንዲህ እ... ጠይቆኛል እንዲህ በማለት፡ “ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ እዚህስ ሊያገጥም ይችላልን? ” እይ፡ አላውቅም። እስከ ማውቀው ድረስ፡ አላውቀውም። በእውነት።

15 ሁልጊዜ ለእናንተ ቅን መሆን እፈልጋለው። መገመት፡ የሆነ ሃሳብ፡ ወይም የሆነ በግሌ የማምነውን ነገር፡ ወይም እንደዛ ያለ ነገር፡ እንደዛ አላደርግም። እኔ በምናገርበት ጊዜ፡ ይፈጸማል። ስለዚህ፡ በመጀመሪያ፡ እርሱ ለእኔ ይነግረኛል፡ እኔም ለእናንተ እነግራችኋለው። ዓለም በሙሉ በፍርሃት ውስጥ እንዳለ እ—አውቃለሁ። በመጨረሻው ዘመን ላይ ነን። ነገር ግን ለመሆን የሞከርኩት አንድ ነገር...

16 ወንድም ሻካሪያን ዛሬ ጠዋት፡ እንዴት ወደ ጸሎት ስልፍ ሄደ፡ ሰዎችም ከመምጣታቸው በፊት ካርዶቹን ወሰደ፡ እንደተመለከታቸውና፡ እዚያ ላይ የጻፉትን ነገር እ—እነግራቸው እንደሆነ እያዬ እንደነበረ እየነገረኝ ነበር። በጸሎት ካርዶቻቸው ላይ ሁሉንም ዓይነት ነገሮች ይጽፋሉ፡ ታውቃላችሁ፡ እርሱም ያ ትክክል መሆኑን ለማየት ብቻ ፈለገ። ከፈተሻቸው በመቶዎች ከሚቆጠሩ መካከል፡ አንድም ስሕተት ሆኖ እንዳልተገኘ፡ ተናግሯል። ምክንያቱም፡ እግዚአብሔር እስከሆነ ድረስ፡ አንድም ስሕተት እ—አይኖረውም፡ አያችሁ። ራሴን እዚያ ውስጥ ካስገባሁት፡ ገና ከጅምሩ በዚያች ቅጽበት ስሕተት ይሆናል።

17 አንዲት ትንሽ ልጅ በቅርቡ፡ ወደ እኔ መጣች፡ እና አሁን አባቷ ቁጭ ብሎ፡ እያዳመጠኝ ነው። ሕልም አይታ ነበር። እንዲህ አለችኝ፡ “ወንድም ብራንሃም፡ ይህ ሕልም ምን ማለት ነው? ”

18 እኔም፡ “እህቴ፡ አላውቅም። እግዚአብሔር የሚነግረኝ እንደሆነ፡ ማወቅ አለብኝ” አልኳት። ስለዚህ ሄጄ ጌታን ለመጠየቅ ሞከርኩ፡ እርሱም በጭራሽ አልነገረኝም።

19 ትንሿ ልጅ ተመልሳ መጣች። እርሷም፡ “መልካም፡ አሁን የህልሜ ትርጓሜ የት አለ” አለች?

20 እኔም፡ “ወደዚህ ነይ፡ ማር፡ ቁጭ በይ” አልኳት። እኔም፡ “አባትሽና እናትሽ በጣም ጥሩ ጓደኞቼ ናቸው። አየሽ? ከካናዳ ያንን ሁሉ መንገድ መጥተው፡ ጡረታ ወጥተው፡ አሁን ከእኔ ጋር እዚህ እየኖሩ ነው። እነርሱም እኔ የምላቸውን፡ ይህ ሁሉ ያምናሉ። እኔም በሕይወቴ፡ ሆን ብዬ፡ ለማንም የተሳሳተ ነገር ተናግሬ አላውቅም። የሕልሙ... ትርጉም እውቄዋለሁ ብዬ አስባለው። ይሁን እንጂ ሕልሙን ራሴ እስካላየሁና፡ ከዚያም ትርጉሙን እስካልነገረኝ ድረስ፡ ልነግርሽ አልችልም። እየሽ፡ አንድ ነገር ፈጥሬ ብናገርል፡ በሕይወት እና በሞት መካከል የምትፈልጊበት ጊዜ ሊኖር ይችላል፡ ከዚያም እኔን ማመን ወይም አለማመንን እንዳለብሽ አታውቂም” አልኳት።

21 ምንም ነገር በጌታ ስም ከነገርኳችሁ፡ እውነት መሆኑን ነው። ያ ነው የነገረኝ። እስካሁን ድረስ፡ በእነዚህ ሁሉ ዓመታት ውስጥ፡ በመላው ዓለም፡ እና በዓለም ዙሪያ፡ አንድ ጊዜ ስሕተት ሆኖ አያውቅም። ምክንያቱም... አሁንም፡ አንድ ሰው ይህን ያህል የማይሳሳት ሊሆን እንደማይችል፡ ታውቃላችሁ። ይህን ለማድረግ የእግዚአብሔር መንፈስ ያስፈልጋል።

22 አሁንም ኃላፊነት የምሸከምበት መልዕክት አለኝ። ብዙ ጊዜ በሰዎች መካከል፡ ግምት ውስጥ ገብቻለው፡ እንግዲህ፡ ምናልባት ሰው፡ ለአፍታ ቁጭ ብሎ ሳያስብ፡ ኦህ፡ እ—እስከፊ ሰው እንደሆንኩ፡ ሰዎችን እንደማልወድና፡ ሁልጊዜ እነሱን እንደምቆርጣቸው አድርጎ ይገምታል። እንደዚያ አይደለም። ያ ትክክል አይደለም። ሰዎችን እወዳቸዋለሁ። ነገር ግን፡ ታውቃላችሁ፡ ፍቅር አራሚ ነው።

23 ህጻኑ ልጃችሁ ውጪ መንገድ ላይ ቢቀመጥ፡ እናንተም እንዲህ ትሉታላችሁ፡ “ልጄ፡ ውዴ፡ በዚያ ውጪ እንድትቀመጥ አልፈልግም፡ ግን... ” መኪኖች ሲጮኹበት፡ ወደ ውስጥ ታስገቡታላችሁ። እንደገናም ወደ

ውጭ ይሮጣል። ያን ጊዜ፡ ልታርሙት ይገባችኋል። የምትወዱት ከሆነ፡ ታርሙታላችሁ። ይህን ማድረግ አለባችሁ።

24 አንድ ሰው በጀልባ ወንዝ ላይ እየተንሳፈፈ፡ ወደ ፏፏቴ፡ የሚሄድ ሰው ብታዩት፡ ጀልባው ፏፏቴውን ሲነካ እንደሚሰምጥ ካወቃችሁ፡ "ጆን፡ አንተ፡ ምናልባት ትንሽ ቆም ብለህ ማሰብ አለብህ፡ ምናልባት ላትተርፍ ትችላለህ፡" ትሉታላችሁን? እንደማይተርፍ ካወቅኩኝ፡ ከቻልኩ፡ ከጀልባው አውጥቼ ልወረውረው እችላለሁ፡ ምክንያቱም ይህን የሚያደርገው ፍቅር ስለሆነ ነው።

25 አሁንም፡ በምናገራቸው በእነዚህ መልዕክቶች ውስጥ፡ ምንም ዓይነት ዶክትሪን፡ ወይም ሌላ ነገር ለማምጣት ፈጽሞ አልሞክርም። ይህን የ— የማደርገው በራሴ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው። ነገር ግን የተለያዩ ሃይማኖቶችና ሃሳቦች ባሏቸው ወንዶችና ሴቶች መካከል ሆኜ፡ በገርነት ለመናገር፡ ለማብራራት እሞክራለሁ፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር መንፈስ የተወለዳችሁ ከሆናችሁ፡ በክርስቲያን ሰዎች በሜቶዲስት በባፕቲስት፡ በፕሬስባይቴሪያን፡ በሌሎችም መካከል፡ ምን ማለቴ፡ እንደሆነ፡ ትረዳላችሁ-ብዬ አምናለሁ።

26 አሁን፡ ዛሬ ማታ፡ ወደ ዘፍጥረት ምዕራፍ 24፡ መሄድ እፈልጋለሁ። በ... ዘፍጥረት ምዕራፍ 24 ጀምሬ ቊጥር 12 ላይ የሚገኘውን ሃሳብ ማንበብ እፈልጋለሁ።

> **እንዲህም አለ፡ የጌታዬ የ... አብርሃም አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፡ እለምንሃለሁ፡ መንገዴን ዛሬ በፊቴ አቅናልኝ፡ ለጌታዬም ለአብርሃም ምሕረትን አድርግ።**
>
> **እነሆ፡ በዚህ የውኃ ምንጭ አጠገብ እኔ ቆሜአለሁ፣ የዚህችም ከተማ ሴቶች ልጆች ውኃውን ሊቀዱ ይመጣሉ፥**
>
> **ውኃ እጠጣ ዘንድ፡** እንስራሽን **አዘንብዪ፡ የምላት፡ እርሰዋም፥ አንተ ጠጣ፡ ግመሎችህን ደግሞ አጠጣለሁ፡ የምትለኝ ቆንጆ፡ እርሰዋ ለባሪያህ ለይስሐቅ** ያዘጋጀሃት **ትሁን፣ በዚህም ለጌታዬ** ምሕረትን **እንዳደረግህ** እ... **አውቃለሁ።**

27 በመቀጠል በራእይ መጽሐፍ ላይ እንከፍታለን። ዘፍጥረት፡ የመጽሐፍ ቅዱስ መጀመሪያው ነው። አሁን፡ በመጨረሻው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ፡ በራእይ ምዕራፍ 21፡ ከቁጥር 9 ላይ ያለውን ማንበብ እፈልጋለሁ።

28 ይህ ያነበብነው የዘፍጥረት መጽሐፍ ጥቅስ ምን እንደሚል እናውቃለን... ከፈለጋችሁ፡ ሙሉውን ምዕራፍ አንብቡ። ኤሊዔዘርን የላከው እግዚአብሔር ነው። ይቅርታ አድርጉልኝ፡ ወይንም፡ አብርሃም ኤሊዔዘርን፡ ለይስሐቅ ሙሽራ እንዲመርጥ ልኮታል። ቆንጆዋ ርብቃም መጣች፡ የአብርሃም አገልጋይ፡ ኤሊዔዘር፡ ላቀረበው ጸ—ጸሎትም ፍጹም መልስ ሆነች።

አሁን ደግሞ በራእይ ምዕራፍ 21 ቊጥር 9 ላይ እንከፍታለን።

> **ሰባቱም ኋለኛዎች መቅሠፍቶች የሞሉባቸውን ሰባቱን ጽዋዎች ከያዙት ከሰባቱ መላእክት አንዱ መጥቶ፡ ወደዚህ ና፡** የበጉንም **ሚስት፡ ሙሽራይቱን፡ አሳይሃለሁ፡ ብሎ ተናገረኝ።**

29 አሁን ዛሬ ማታ፡ እንደ ርዕስ፡ የምወስደው፥ **የሙሽራ አመራረጥ** የሚለውን ነው። ይህን የሚቀዳው ወንድሜ፡ ከቀዳው፡ ቀድመህ ማስራጨት ያለብህ ይህን መልዕክት ነው።

30 አሁንም፡ በዚህ ውስጥ፡ ይህንን በትክክል የምናገረው ለዚህ ጉባኤ ነው ማለት አይደለም፡ ነገር ግን እነዚህ ቴፖች በዓለም ዙሪያ ይሄዳሉ። ኦህ፡ በተግባር፡ በብዙ ቋንቋዎች፡ በዓለም ዙሪያ ወደ አረማውያን አገሮች ሳይቀር፡ ተተርጉመዋል። ለቤተክርስቲያን ማኅበር፡ ቴፖችን፡ በነፃ እንልክላቸዋለን። እነርሱም የተተረጎሙ ናቸው። እና በአፍሪካ ጫካዎች ሁሉ፡ ወደ ህንድ፡ በዓለምም ዙሪያ፡ እነዚህ ቴፖች ይሄዳሉ።

አሁን፡ የሙሽራ አመራረጥ!

31 በሕይወት ውስጥ በብዙ ነገሮች ምርጫ ተሰጥቶናል። የሕይወት መንገድ፡ በራሱ፡ ምርጫ ነው። የራሳችንን መንገድ የመምረጥ መብት አለን፡ የምንኖርበትን መንገድ የመምረጥ መብት አለን።

32 ትምህርት ምርጫ ነው። መማር ካለብን እንመርጣለን፡ ወይም አለመማር መምረጥ እንችላለን። ያ ያለን ምርጫችን ነው።

33 ትክክል እና ስሕተት ምርጫ ነው። ሁሉም ወንዶች፡ ሁሉም ሴቶች፡ ልጅ እና ልጃገረድ፡ በትክክል ለመኖር ወይም ላለመኖር መምረጥ አለባቸው። ምርጫ ነው።

ምርጫ ታላቅ ነገር ነው።

34 ዘላለማዊ መድረሻችሁ ምርጫችሁ ነው። ምናልባት፡ ዛሬ ማታ፡ እንዳንዶቻችሁ ይህ አገልግሎት ከ—ከማለቁ በፊት፡ ዘላለማችሁን የት እንደምታሳልፉት፡ ያንን ምርጫ ታደርጋላችሁ። እግዚአብሔርን ደግጋማችሁ የምትክዱት ከሆናችሁ፡ እግዚአብሔርን ለመጨረሻ ጊዜ፡ የምትክዱበት፡ ጊዜ ይመጣል። በምሕረት እና በፍርድ መካከል መስመር አለች። ለወንዱም ለሴቷም፡ ለአባወራውም እማወራዋም፡ ያንን መስመር ማለፍ አደገኛ ነገር ነው፡ ምክንያቱም ያንን የጊዜ ገደብ ካቋረጡ በኋላ መመለስ አይቻልም። ስለዚህ፡ ዛሬ ማታ፡ ብዙዎች መጨረሻ የሌለውን ዘላለማዊነትን የ—የሚያሳልፉበትን፡ ውሳኔያቸውን የሚወስኑበት ጊዜ ሊሆን ይችላል።

35 ሌላም በሕይወታችን ውስጥም ሌላ ምርጫ አለን፡ ይህም፡ የሕይወት አጋር ምርጫ ነው። አንድ ወጣት ወንድ ወይም ወጣት ሴት፡ በሕይወቱ ውስጥ፡ ምርጫ የ—የማድረግ መብት ተሰጥቶታል። ወጣቱ ይመርጣል። ወጣቷ ሴት የመቀበልም ሆነ የመቃወም መብት አላት። ነገር ግን አሁንም ቢሆን በሁለቱም ወገኖች፡ ምርጫ ነው። ወንዶችም ሆኑ ሴቶች፡ የመምረጥ መብት አላቸው።

በተጨማሪም፡ ክርስቲያን እንደመሆናችሁ መጠን፡ ምርጫ አላችሁ።

36 እዚህ አሜሪካ ውስጥ፡ እስካሁን ድረስ፡ መሄድ የምትችሉትን፡ ቤተክርስቲያን መምረጥ ትችላላችሁ። የፈለጋችሁትን ቤተክርስቲያን መምረጥ፡ አሜሪካዊ መብታችሁ ነው። ምርጫ ነው። የማትፈልጉ ከሆነ፡ ወደ አንዳቸውም መሄድ የለባችሁም። ነገር ግን ከሜቶዲስት ወደ ባፕቲስት፡ ከካቶሊክ ወደ ፕሮቴስታንት፡ ወዘተ፡ መሄድ ከፈለጋችሁ ማንም ሊነግራችሁ ወይም ወደ አንድ የተወሰነ ቤተክርስቲያን እንዲትመጡ ሊያደርጋችሁ

አይችልም። ይህ—ነፃነታችን ነው። ዴሞክራሲያችን እንዲህ ነው። እያንዳንዱ ሰው ለራሱ መምረጥ ይችላል። የሃይማኖት ነጻነት፡ ት—ትልቅ ነገር ነው። በተቻለን መጠን እንድናቆየው እግዚአብሔር ይርዳን።

37 እናንተም ምርጫ አላችሁ። ይ... ይህን ቤተክርስቲያን ስትመርጡ፡ በዚህ ቤተክርስቲያን፡ ወደ ዘለዓለማዊ መድረሻችሁ፡ የሚመራችሁ ቤተክርስቲያንን መምረጥ ትችላላችሁ። የሃይማኖት መግለጫው የምፈልገው ነገር ነው ብላችሁ በማሰብ፡ አንዲት የሃይማኖት መግለጫ ያላትን ቤተክርስቲያን ልትመርጡ ትችላላችሁ። ወይም፡ ደግሞ ሌሎች ቤተክርስቲያን የራሳቸው የሃይማኖት መገለጫ አላቸው።

38 ከዚያም ምርጫ ማድረግ ያለባችሁ፡ የእግዚአብሔር ቃል አለ። መምረጥ አለባችሁ።

በመካከላችን የመምረጥ ሕግ የሚባል፡ ያልተጻፈ ሕግ አለ።

39 አንድ ጊዜ፡ ኤልያስ ይመስለኛል፡ በቀርሜሎስ ተራራ ላይ፡ ከትዕይንቱ በኋላ፡ ልክ አሁን ወደ እኛ ሊመጣ እንዳለው ታላቅ የችግር ሰዓት ነበር። ምናልባትም፡ ዛሬ ማታ፡ አንተ ወይም እኔ፡ ይህንን ምርጫ፡ እንደ ቀርሜሎስ ተራራ ተሞክሮ እናደርጋለን። እውነቱን ለመናገር፡ አሁን በዓለም ዙሪያ፡ እየተካሄደ ያለ፡ ይመስለኛል። ነገር ግን በቅርቡ አንድ ምርጫ ማድረግ ያለባችሁ ጊዜ ይመጣል።

40 እናንተም እዚህ ያላችሁ፡ የሃይማኖት ተቋም ቤተክርስቲያኖቻችሁ፡ ምርጫ በሚታደርጉበት ጊዜ፡ ሰዓቱ ትክክል እንደሆነ፡ ይህን ብቻ እመኑ። ወይ ወደ ዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጥምረት ትቀላቀላላችሁ፡ ወይም ደግሞ የሃይማኖት ተቋም መሆናችሁ ይቀራል። ይህን ማድረጋችሁ የማይቀር ነውና፡ ያ ምርጫ በቅርቡ ይመጣል።

41 እስከዚያውም መጨረሻ ሰዓት ድረስ መጠበቅ፡ አደገኛ ነገር ነው፡ ምክንያቱም በጭራሽ መውጣት ወደማትችሉበት ነገር ውስጥ ሊትገቡ ትችላላችሁ። ታውቃላችሁ፡ ማስጠንቀቂያ ሊሰጣችሁ የሚችልበት ጊዜ አለ፡ ከዚያም፡ ያንን የማስጠንቀቂያ መስመር ካቋረጣችሁ፡ ከዚያ በሌላው በኩል ምልክት ይደርግባችኋል፡ የሌላኛው ጎን ተወካይ ትሆናላችሁ።

42 አስታውሱ፡ የኢዮቤልዩ ዓመት ሲመጣ፡ ካህኑ መ—መለከቱን እየነፋ ሲጋልብ፡ እያንዳንዱ ባሪያ ነጻ መውጣት እንደሚችል አስታውሱ። ነገር ግን ነጻነታቸውን ለመቀበል ፈቃደኛ ካልሆኑ፡ በቤተ መቅደሱ ወዳለው፡ ወደ አንድ ምሶሶ ይወሰዳሉ፡ በዚያም ጆሮው በመብሻ ይበሳልና፡ ከዚያ ጌታውን ሁልጊዜ ያገለግላል። በጆሮው ላይ የመሰማት፡ ምልክት ሆኖ ይቀመጣል። “እምነት የሚመጣው በመስማት ነው።” መለከቱን ሰምቷል፡ ይሁን እንጂ ማዳመጥ አልፈለገም።

43 እናም ብዙ ጊዜ፡ ወንዶችና ሴቶች የእግዚአብሔርን እውነት ሲሰሙ፡ እውነታው ሲታይ እና ሲረጋገጥ፡ እየተመለከቱ፡ ነገር ግን መስማት አይፈልጉም። ሌላ ምክንያት አለ። እውነትና ሃቅ የሆነውን ከመጋፈጥ ይልቅ፡ ሌላ ምርጫ አላቸው፡ ስለዚህ ጆሮዎቻቸው ለወንጌል ዝግ ሊሆኑ ይችላሉ። ደግመው አይሰሙትም። የምመክራችሁ፡ እግዚአብሔር ለልባችሁ ሲናገር፡ ወዲያውኑ እርምጃ መውሰድ አለባችሁ።

44 ኤልያስ አንድ ምርጫ ሰጣቸው፡ እነሱም መምረጥ ነበረባቸው፡ “የሚታገለግሉትን ዛሬውኑ ምረጡ። እግዚአብሔር አምላክ ከሆነ፡ እሱን አምልኩት። ባአል አምላክ ከሆነ ግን፡ እሱን አምልኩት።

45 አሁን፡ እንደምናየው ሁሉም የተፈጥሮ ነገሮች የመንፈሳዊ ነገሮች ተምሳሌት ናቸው፡ ዛሬ ጠዋት ፀሐይና ተፈጥሮዋ፡ የሚል ትምህርት እንደተማርነው ዓይነት ነው። የመጀምሪያው መጽሐፍ ቅዱሴ ያ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስን አንድ ገጽ እንኳ ሳላነብ፡ እግዚአብሔርን አውቀዋለሁ። ምክንያቱም፡ መጽሐፍ ቅዱስ በተፈጥሮ ውስጥ በሁሉም ቦታ ተጽፏል፡ ከእግዚብሔር ቃል ጋር ይዛመዳል፡ ሞት፡ ቀብር፡ የተፈጥሮ ትንሣኤ፣ ፀሐይ ስትወጣ፡ ስትሻገር፡ ስትጠልቅ፡ ስትሞት፡ እንደገና ስትወጣ ከእግዚብሔር ቃል ጋር ይዛመዳል። እግዚአብሔርን በተፈጥሮ ውስጥ፡ ልናስመስለው የምንችላቸው ብዙ ነገሮች አሉ፡ አሁን ይን ትተን፡ በዛሬው መልዕክት ላይ ትኩረት እናድርግ።

46 አሁን፡ መንፈሳዊው፡ ወይም፡ ተፈጥሯዊው የመንፈሳዊው ምሳሌ ከሆነ፡ ከዚያም፡ በተፈጥሯዊው፡ ሙሽራን መምረጥ፡ በመንፈሳዊው፡ ሙሽራ የመምረጥ፡ ምሳሌ ነው።

47 አሁን፡ ወደ ሚስት አመራረጥ ስንገባ፡ አንድ ወንድ “ሞት እስኪለየን ድረስ፡” ብሎ ቃል ስለሚገባ ጥብቅ ጉዳይ ነው። በዚህ መልኩ መጠበቅ አለብን። ይህን ቃል ኪዳን በእግዚአብሔር ፊት ትገባላችሁ፡ ሞት ብቻ ነው የሚለያችሁ። እኛም ማድረግ ያለብን… የወደፊት እቅድ የሚያወጣ፡ ጤናማ አእምሮ ያለው ሰው፡ ሚስት በጥንቃቄ መምረጥ አለበት። የምታደርጉትን ነገር በጥንቃቄ አድርጉ። እንዲት ሴት ባሏን ስትመርጥ፡ ወይም የባሏን ምርጫ ስትቀበል፡ በተለይ በዚህ ዘመን፡ ለሚታደርገውን ነገር ጥንቃቄ ማድረግ አለባት። አንድ ሰው ሚስት ከመምረጡ በፊት ማሰብና መጸለይ ይኖርበታል።

48 እንደማስበው፡ ዛሬ፡ ብዙ የ… የፍቺ ጉዳዮች ስለበዙ፡ በፍቺ ጉዳዮች፡ እኛ አሜሪካ በብዛት አለምን እየመራን ነው። እኛ የቀረውን ዓለም እየመራን ነው። በዚህ ሀገር ውስጥ፡ ከሌላው ከማንኛውም ቦታ የበለጠ ፍቺዎች አሉ፡ መሆንም ነበረበት፡ ክርስቲያን ሃገር ተብሎ፡ ይታሰባል። የፍቺ ፍርድ ቤቶቻችን፡ ምንኛ ውርደት ናቸው! እንደማስበው፡ ምክንያቱ፡ ወንዶች ከእግዚአብሔር ስለራቁ፡ ሴቶችም ከእግዚአብሔር ስለራቁ ነው።

49 ይህን፡ እናውቃለን፡ አንድ ወንድ ቢጸልይ እና እንዲት ሴት በጉዳዩ ላይ ብትጸልይ፣ የሚያምሩ ዓይኖችን፡ ወይም ትልልቅ ጠንካራ ትከሻዎችን፡ ወይም እንደዚህ ያሉትን፡ ወይም ሌላ ዓለማዊ ፍቅርን መመልከት ሳይሆን፣ በመጀመሪያ ወደ እግዚአብሔር ይመልከቱ፡ እንዲህም ይበሉ፡ “እግዚአብሔር ሆይ፡ እቅድህ ምንድነው?”

50 እንደሚመስለኝ፡ ዛሬም፡ ልክ እንደ ትምህርት ቤት ኩረጃ፡ ብዙ ማጭበርበር አለ። ል—ልጆች፡ ማልደው ይመጡና፡ ብዙዎቹ የጎሮበት ልጆች፡ የጓደኞቼ—ልጆች ናቸው፡ ይመጡና እንዲህ ይላሉ፡ “ወንድም ብራንሃም፡ ለእኛስ ትጸልይልናለህ? ዛሬ—ፈተና አለብን። ሌሊቱን በሙሉ አ—አጥንቻለሁ፡ ጥሩ ውጤት የማገኝ አ—አይመስለኝም። ጸልይልኝ።” እንደማስበው፡ ማንኛውም የ… የትምህርት ቤት ልጅ… ወላጆች ጠዋት በጠረጴዛው ላይ፡ “እናቴ፡ ጆን ዛሬ ፈተና አለው። አሁን እንጸልይለት፡”

ማለት አለባችሁ። እንደማስበው የሌላ ሰው ወረቀት ከማየትና ከመኮረጅ ይልቅ፥ እንደሚመስለኝ፥ ወጥታችሁ ብትጸልዩ፥ በሌላ መንገድ ሊታደርጉት ከሚትችሉት ነገር ሁሉ ይበልጣል።

51 ትዳር ስንመሰርትም ምን እየሰራን እንደሆነ ብናጠና፥ ሚስት ስንመርጥ፥ ባል ስንመርጥ፥ የምናደርገውን ነገር በጥንቃቄ ብናጠና ኖሮ! አንድ ሰው አጥብቆ መጸለይ አለበት፥ ምክንያቱም መላ ሕይወቱን ሊያበላሸው ይችላል። አስታውሱ፥ ቃልኪዳኑ "ሞት እስኪለየን ድረስ" ነው፥ የተሳሳተ ምርጫ በማድረግ ሕይወቱን ሊያበላሸው ይችላል። የተሳሳተ ምርጫ እንደሚያደርግ፥ ሚስቱ ለመሆን ብቁ ያልሆነችውን ሴት እንደሚያገባ ካወቀ በኋላ፥ እንዲሁ ዝም ብሎ የሚያገባት ከሆነ፥ ይህ የራሱ ጥፋት ነው። ሴት ባሏን አይታ ባልሽ ለመሆን ብቁ እንዳልሆነ ካወቅሽ በኋላ የሚታገቢ ከሆነ፥ ስሕተት የሆነውን ካወቅሽ በኋላ ካገባሽ፥ ያ የራስሽ ጥፋት ነው። ስለዚህ፥ በደንብ እስካልጸለየላችሁ ድረስ ማድረግ የለባችሁም።

52 ቤተ ክርስቲያንን በመምረጥ ረገድም ሁኔታው ተመሳሳይ ነው። አሁን፥ ህብረት በሚታደርጉበት በቤተክርስቲያናችሁ ላይ መጸለይ አለባችሁ። አስታውሱ፥ አብያተ ክርስቲያናት የሚሸከሙት መንፈስ አለ።

53 አሁን፥ እኔ ተቺ መሆን አልፈልግም። ነገር ግን ሽማግሌ መሆኔን ተገንዝቤአለሁ፥ በእነዚህ ቀናቶች፥ ምድር ትቼ እንደሚሄድ አውቃለሁ። ዛሬ ማታ ወይም ሌላ ጊዜ ስለ ተናገርኩት ነገር ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ እሰጥበታለሁ። እኔም፥ ስለዚህ፥ በጣም እውነተኛ እና በእውነት የተሰጠ ሰው መሆን ይጠበቅብኛል።

54 ነገር ግን፥ ወደ ቤተክርስቲያን ስትገቡ፥ የቤተክርስቲያንቷን ባህርይ ብትመለከቱ፥ ፓስተሩን ለተወሰነ ጊዜ ብትመለከቱ፥ ቤተክርስቲያን እንደ ፓስተሩ እንደምታደርግ ታውቃላችሁ። አንዳንድ ጊዜ፥ ከመንፈስ ቅዱስ ይልቅ እንዳችን የሌላውን መንፈስ የምንቀበል መሆናችንን ራሴን እጠይቃለሁ። አንድ ፓስተር በጣም አክራሪ ከሆነ እና እንዲሁ ሲንፈራገጥ ካያችሁ፥ ጉባኤውም በተመሳሳይ መንገድ መሆኑን ታገኛላችሁ። ፓስተሩ ቆሞ ራሳቸውን ወደ ፊትና ወደ ኋላ የሚወዘውዙበት፥ ቤተክርስቲያን ላምጣላችሁ። ጉባኤውም፥ ተመሳሳይ ነገር ያደርጋሉ። አንድ ፓስተር፥ ማንኛውንም ነገር የሚበላ ከሆነ፥ ቤተክርስቲያኑም ተመሳሳይ ነገር ያደርጋል። ስለዚህ፥ ቤተክርስቲያንን ከመረጥኩ፥ ቤተሰቤን ለማስገባት፥ እውነተኛ፥ መሰረታዊ፥ ሙሉ ወንጌል ያላት፥ እውነተኛ የሆነውችን እመርጣለሁ። ምረጡ። ተመለከትሁ...

55 ልጆቹ፥ በቀደም፥ የወንድም ሻካሪያን ልጅና የ-አማቱ-ልጅ፥ ለወጣቱ ዘማሪ፥ ለቆንጆ ልጅ፥ ለመጸለይ ወደዚህ ወሰዱኝ። ልክ ተመልሶ መጣ... ፍሬድ ባርከር፥ ስሙ ይህ ነበር፥ ከጉዞ ተመልሶ መጣ። እነሱም፥ "ፍሬድ እየሞተ ነው፥" ብለው ደወሉልኝ። ከዚያም፥ ወደ ቤት ከመግባቴ በፊት፥ ሌላ መልእክት መጣ፥ "አሁን ሞቶ ሊሆን ይችላል" የምል። የአንጎል ደም—መፍሰስ እንደደረሰበትና፥ ሽባ እንደሆነ፥ እ—እየሞተ እንደነበረ፥ ሚስቱም እንድጸልይለት እንደፈለገች ነገረኝ።

56 እንዲህም ብዬ አሰብኩ፥ "ኦ፥ ለመብረር ብሞክር፥ እዚያ ከመድረሴ በፊት ሊሞትይችላል፥ ምናልባትም አሁን ሊሞት ይችላል።" ስለዚህ፥ በፍጥነት

ስልክ ደወልኩና ምስኪን ሴት አገኘኋት። እ—እና ስልኩን፡ በፍሬድ ጆሮ አደርገነው። መዋጥ አይችልም ነበር። ሰው ሠራሽ የመዋጫ ቱቦ አድርገውበት ነበር። ከጸለይንለት በኋላ፡ በምልክት፡ እንዲህ አለ፡ ሰው ሰራሹን ከጉሮሮው እንድናወጣ ነገረን። መዋጥም ቻለ። ዶክተሮቹም አላመኑም። እነርሱም አወጡትና፡ መዋጥ ቻለ። በቀደምእለታ፡ ቀና ብሎ ተቀምጦ ነበር።

ቤተክርስቲያን፣ ቤተክርስቲያንን መምረጥ።

57 ከጥቂት ጊዜ በፊት፡ ስልክ ብቻ ተደወለልኝ። ዛሬ ጠዋት፡ የቤተክርስቲያኔ አባል የሆነች፡ የሉዊቪል ተወላጅ የሆነች ባፕቲስት ሴት፡ ዛሬ ጠዋት ሞተች። በቤቴም የነበረችው ቤተ ክርስቲያን፡ እውነተኛ የሃይማኖት ተከታይ የሆኑ ሰዎች፡ የቀብር አስፈጻሚው፡ አስከሬኗን ከመገነዙ በፊት ተሰብስበው ሄዱ፡ በአጠገቧ ሆነው፡ ወደ ሕይወት እስክትመለስ ድረስ ጸለዩ። ዛሬ ማታ፡ በሕይወት አለች። ምክንያቱም፡ የቤተክርስቲያናችን ሽማግሌዎች፡ ሁሉም ነገር እንደሚቻል፡ ወደ እግዚአብሔር በቅንነት መምጣት እንዳለባቸው ተምረዋል።

ስለዚህ፡ ትክክለኛውን ምርጫ ማድረግ አለባችሁ።

58 በድጋሜ፡ አንድ ወንድ የሚመርጠው የሴት አይነት፡ የእርሱን ምኞትና ባህሪ የሚያንጸባርቅ ነው። አንድ ወንድ የተሳሳተ ሴትን ከመረጠ፡ ባህሪውን ያንጸባርቃል። ራሱን የሚያስተሳስረው ነገር፡ በውስጡ ያለውን ነገር በግልጽ ያሳያል። አንዲት ሴት አንድ ሰው ሚስቱ አድርጎ ሲመርጣት በውስጡ ያለውን ነገር ታንጸባርቃለች። በውስጡ ያለውን ነገር ያሳያል። በውጪ እሱ የምናገረው ምንም ይሁን ምን፡ ያገባትን ተመልከቱ።

59 ወደ አንድ ክርስቲያን ነኝ ባይ ሰው፡ ቢሮው ውስጥ ገባሁና፡ የራቁታም ሴቶች ስዕል በግድግዳዎች ዙርያ ተለጥፈው፡ የድሮ ቡጊ-ዎጊ ሙዚቃ ተከፍቶ ነበር። እሱ ምንም ቢል ግድ የለኝም። የእርሱን ምስክርነት አላምንም፡ ምክንያቱም መንፈሱ በእነዚያ በዓለም ነገሮች ላይ እየተመገበ ነው። ምን፡ እንበል፡ የሚትጨፍር ልጅ ቢያገባ፡ ወይም የወሲብ ንግሥት ቢያገባ፡ ወይም ቆንጆ፡ ወይም ዘመናዊ ቀበጥ ቢያገባስ? ይህ የሚያንጸባርቀው፡ በአዕምሮው ውስጥ ያለውን ያሳያል፡ የወደፊቱ ቤቱ ምን እንደሚሆን፡ ምክንያቱም ልጆቹን ለማሳደግ ነው ያገባት። እሷ ምንም ትሁን ምን፡ ልጆቹዋን የምታሳድገው በዚያው መንገድ ነው። ስለዚህ፡ በወንዱ ውስጥ ያለውን ታንጸባርቃለች። እንደዚህ ዓይነት ሴት የሚይዝ ሰው፡ ስለወደፊቱ ምን እንደሚያስብ ያሳያል።

60 አንድ ክርስቲያን እንዲህ ያለ ድርጊት እንደሚፈፅም መገመት ትችላላችሁ? አይ፡ ወዳጄ። አልችልም። እውነተኛ ክርስቲያን እንደዚያ አይነት የውበት ንግስቶችንና፡ ጨፋሪ ሴቶችንና፡ የወሲብ ንግስቶችን አይፈልግም። ክርስቲያናዊ ባህርይ ይፈልጋል።

61 አሁን፡ ሁሉንም ነገር ማግኘት አትችልም፡ በጣም ቄንጀ የሆነች ልጃገረድ ልትኖር ትችላለች፡ ሌላ ልጃገረድ፡ ምናልባት እሷ፡ ቁመናዋ **ከዚችኛዋ** የተሻለ ሊሆን ይችላልና፡ አንዷን ለሌላዋ መሥዋዕት ማድረግ ሊኖርብህ ይችላል። ነገር ግን የሴት፡ ወይም የሴት ቁመና፡ ከሌላት... ቄንጆ ብትሆንም ባትሆንም፡ ባሕርይዋን ብትመለከት ይሻላል፡ ቆንጆ ብትሆንም ባትሆንም።

62 አሁን፡ አንድ ክርስቲያን፡ ሚስት ለመምረጥ ከፈለገ፡ ምንም ትምስል ምን፡ እውነተኛ፡ ዳግመኛ-የተወለደች ሴት፡ መምረጥ ይኖርበታል። ማንነቷ ነው፡ ራሷን

የሚያደርጋት። ከዚያም፡ እንደገና፡ ያ የራሱን አምላካዊ ባህሪ ያንጸባርቃልና፡ በአዕምሮው ውስጥ ያለውንና ለወደፊቱ ምን እንደሚሆን ያንጸባርቃል፡ ለወደፊቱ የቤቱ እቅድ፡ ቤተሰቡ በእንደዚህ ዓይነት ሴት እንደሚያድግ ያሳያል።

63 ከእነዚህ ምስኪን ዘመናዊ ቀበጦች፡ የወሲብ ንግሥቶች፡ አንዷ ካገባ ምን ይጠብቃል? ይህ ሰው ምን ዓይነት ቤት ሊኖረው ይችላል? ቤት መቈየትና ቤቱን ለመንከባከብ ለራሷ በቂ ሞራል የሌላትን ካገባ፡ ቢሮ ውስጥ መሥራት የምትፈልግ ከሆነች፡ ምን ዓይነት የቤት እመቤት ልትሆን ትችላለች? ስለዚህ የልጅ-ሞግዚቶች፡ እና ሌሎች ነገሮች ትቀጥራለህ። እውነት ነው።

64 አሁን፡ እኔ በዚህ ዘመናዊ ሃሳብ፡ ሴቶች ይሰሩ በሚል ሃሳብ አልስማማም። እነዚህ ሴቶች እነዚህን ዩኒፎርሞች ለብሰው፡ በሞተር ብስክሌቶች፡ በዚህ ከተማ ውስጥ ሲዘዋወሩ፡ በፖሊስነት ሲጓዙ ስመለከት፡ አንዲት ሴት እንዲህ እንድታደርግ የሚፈቅድ ለማንኛውም ከተማ ውርደት ነው። እያችሁ? እያችሁ? ሥራ የሌላቸው ወንዶች መብዛታቸው፡ ይህ የከተማችን ዘመናዊ አስተሳሰብ ያሳያል። ውርደቱን ያሳያል። እንደነዚህ ያሉ ሴቶች እዚያ እንዲኖሩ ማድረግ የለብንም። እዚያ እንደዚያ ያለ ምንም ጉዳይ የላቸውም።

65 እግዚአብሔር ለሰው ሚስት ሲሰጥ፡ ከመዳን በስተቀር፡ ሊሰጠው ከሚችለው ሁሉ የላቀውን ነገር ሰጥቶታል። አንድ ሰው የወንድ ቦታ ለመውሰድ ለመሞከር በሚሄድበት ጊዜ፡ እሱ የሚይዘውን ቦታ እርሷ ከያዘች የከፋ ነገር ነው። አሁን፡ ትክክል ነው። እያችሁ?

አሁን መንፈሳዊ አተገባበር ማየት እንችላለን።

66 ይህ መ—መጥፎ እንደሆነ አውቃለሁ፡ እናንተም መጥፎ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ፡ ነገር ግን እውነት ነው። ምንም ያህል መጥፎ ቢሆን ግድ አይሰጠንም፡ እውነታውን መጋፈጥ አለብን። መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረው ይህን ነው። እያችሁ?

67 አሁን፡ እዚህ መንፈሳዊ እቅድ በግልፅ እናያለን፡ እግዚአብሔር ለወደፊቱ ቤቱ ከወደፊቱ ሙሽራው ጋር የሚያደርገው መንፈሳዊ እቅድ፡ አሁን እየታየ ነው።

68 አንድ ሰው አንድ የወሲብ ንግሥት ካገባ፡ ለወደፊት ምን እየፈለገ እንደሆነ ታያላችሁ። አንድ ሰው በቤት ውስጥ የማትቆይ ሴት ካገባ፡ ወደፊት ምን እንደሚፈልግ ታያላችሁ። እኔም አንድ ጊዜ...

69 ይህ በጣም አስከፊ ይመስላል። ለመናገር ስለተሰማኝ ብቻ ነው። አ—አብዛኛውን ጊዜ፡ አንድ ነገር፡ ለማለት ከተሰማኝ፡ እናገረዋለው። አብዛኛውን ጊዜ የእግዚአብሔር መንገድ ነው።

70 ከብት ለ—ለመግዛት፡ አብሬ ከሠራሁት አንድ አርቢ ጋር እሄድ ነበር። ሸማግለው ሰውዬ ጨረታ ከመውጣቱ በፊት ሁል ጊዜ በቀጥታ ወደ ላም ፊት ለፊት እንደሚመለከት አስተዋልኩ። ከዚያም ፊቷን አዙሮ፡ ወደ ፊትና ወደ ኋላ ተመለከተ። እኔም ተከትዬው ሄጄ፡ አየሁት። እርሱም እሷን ወደ ላይ እና ወደ ታች ተመለከተ፡ ጥሩ ቁመና ካላት፡ ደህና መስላ ከታየች ብሎ ተመለከታት። ከዚያም ዞር ብሎ ፊቷን ተመለከተ፡ አንደንድ ጊዜ ጭንቅላቱን እየነቀነቀ አልፎ ይሄዳል።

እኔም፡ “ጃፍ፡ አንድ ነገር ልጠይቅህ እፈልጋለሁ” አልኩት።

እርሱም፡ “ቢል፡ ተናገር” አለኝ።

71 እኔም፡ “ላሟን ሁሌ ፊቷን ለምን ታያታለህ? ” “ደህና ትመስላለች፡ ጥሩ—ጥሩ ከብደት ያላት ላም ትመስላለች” አልኩት።

72 እርሱም “ልጄ፡ ብዙ መማር ያለብህ ነገር እንዳለ፡ ልነግርህ እፈልጋለሁ” አለኝ። ከ—ከነገረኝ በኋላ ተገነዘብኩ። እንዲህ አለ፡ “አቋሟ ግድ አይሰጠኝም። ከራሷ እስከ ሰኮናዋ፡ ሥጋ ብቻ ልትሆን ትችላለች። ነገር ግን ፊቷ ላይ የጭካኔ እይታ ካላት፡ በጭራሽ አትግዛት” አለኝ።

እኔም፡ “ለምን፡ ጄፍ? ” አልኩት

73 “መልካም፡” እኝዲህ አለ፡ “የመልጀመሪያው ነገር፡” አለኝ፡ “እሷ በጭራሽ በአንድ ቦታ አትቀመጥም።” እርሱም፡ “የሚቀጥለው ነገር፡ ለጥጃዋ እናት አትሆንም” አለኝ። አለኝም፡ “ብረት ውስጥ ያሰቀመጧት፡ ወፍራም ስለሆነች ነው። ትፈታታለህ፡ በዛ በዱር እይታ፡ እራሷን ለማጥፋት ትሮጣለች።”

74 እኔም፡ “ታውቃለህ፡ አንድ ነገር ተምሬያለሁ። ይህ ለሴቶችም፡ ይሠራል ብዬ አምናለሁ። ትክክል። በትክክል።

75 የዱር፡ እይታ፡ ሪኬታ እይታ፡ በይኗ ላይ ያ ሁሉ ሰማያዊ ነገር በአይኖቿ ላይ፡ ከእርሷ ብትርቅ ይሻላል፡ ልጄ። አልፈልግም... አልፈልግም። ይህ ለክርስቲያኖች የሚሰማማ አይመስለኝም። በቴሌቪዥን እና በጋዜጦች ላይ ምን ያህል ቄንጆ እንደሆነ ብናገሩ ግድ የለኝም። በሕይወቴ ውስጥ ካየኋቸው እጅግ በጣም አስፈሪ፡ ደሰ-የማይል እይታ ነው።

76 ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁት፡ እዚህ በክሊፍተን ካፌቴሪያ፡ አንድ ቀን ጠዋት፡ ቁርስ እየበላሁ ሳለ... አንዳንድ ወጣት ሴቶች ሲመጡ አየሁ። እኔና፡ ወንድም አርጋንብራይት ወድያው ገባን። እርሱም ደረጃውን ወደ ታች ወርዶ ነበር። እኔም ተመለከትኩ፡ ያችም ልጅ መጣች። እንዲህ አሰብኩ፡ “እንጃ፡ እ—እ—እ— አላውቅም።” ከዚህ በፊት እንዲህ ያለ ነገር አይቼ አላውቅም። የሆነ ዓይነት ነበር። ኦህ፡ የቆሰለች ትመስላለች፡ ታውቃላችሁ፡ የሆነ አሰቂኝ-እይታ ነበራት። ይህን የ—የምለው አሰቂኝ ነገር ለመናገር ሳይሆን፡ ይ—ይህን የምናገረው... ታውቃላችሁ፡ ሚሰዮናዊ እንደመሆኔ መጠን፡ ለምጽ አይቼ አውቃለሁ፡ ሁሉንም አይነት የቆዳ በሽታዎችን አይቻለሁ፡ ታውቃላችሁ፡ በሽታ እንዴት... እንደሆን፡ እኔም ወደ ወጣቷ ልጅ ሄጄ እንዲህ አልኳት፡ “እ... እ... እኔ አገልጋይ ነኝ፡ ለ—ለታመሙት እጸልያለው። እ—እንድጸልይልሽ ትፈልግያለሽ? ” እንደዚህ ያለ ነገር አይቼ አላውቅም ነበር። ከዚያም፡ እነሆ በተጨማሪ ሁለት ወይም ሶስት፡ ገቡ። ከዚያ ወደኋላ ፈቀቅ ብዬ ጠበኩ።

77 ወንድም አርጋንብራይትም መጣ፡ ሰለዚህ እንዲህ አልኩት፡ “ወንድም አርጋንብራይት? ” ምናልባት እዚህ ሊኖር ይችላል። እኔም፡ “የዚያች ሴት ችግር ምንድን ነው” አልኩት? አያችሁ?

እርሱም፡ “ያ፡ ያ ሜካፕ ነው” አለኝ።

78 እኔም “ደህና፡ ማይ፡ ማይ!” አልኩ፡ አያችሁ? ወደ ሌሎች ሁሉም ሴቶች እንዳይተላለፍ፡ ታውቃላችሁ፡ ለብቻዋ ለይቷት የሆነ ቦታ ማሰቀመጥ አለባቸው ብዬ አሰቤ ነበር።

79 ነገር ግን፡ ታውቃላችሁ፡ ስትመርጡ፡ ማቀድ፡ መመልከት፡ መጸለይ፡ አለባችሁ። የተሰፋውን ቃል፡ በዚህ፡ እናያለንና። እሷ፡ ሰው በሚመርጣት ሙሽራ፡ ባህሪውን ታንጸባርቃለች። በውስጡ ያለውን ነገር ያንጸባርቃል።

80 አሁን፡ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሰው፡ እንዲህ ያለች ሴት ሚስቱ እንዲትሆን፡ ሲያገባ ማሰብ አይከብድም? እ—እ—እኔ አይታየኝም፡ ወንድሜ። አሁን፡ ምናልባት እይታዬ ሸማግሌ ሊመስል ይችላል። ነገር ግን፡ ታውቃላችሁ፡ ያ ሊገባኝ አ—አልቻለም፡ እያችሁ፡ እስተውሉ፡ በውስጡ ያለውን ነገር ያንጸባርቃልና። የወደፊት መኖሪያውን ለመገንባት ትረዳዋለች።

81 አሁን፡ ደግሞ፡ ለጊዜው ወደ መንፈሳዊው ገጽታ፡ ስንመለስ። በዓለም ውስጥ ያለች ቤተክርስቲያንን ስታዩ፡ እንደ ዓለም የምትንቀሳቀስ፡ በዓለም ውስጥ የምትጠብቅ፡ ከዓለም የምትካፈል፡ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ፈጽሞ እንዳልጻፋቸው አድርጋ ስትቆጥር ስትመለከቱ፡ ክርስቶስ እንደዚህ ያ—ያለች ሙሽራ እንደማይወስድ መገመት ትችላላችሁ። በዛሬው ጊዜ ያለችውን ቤተ ክርስቲያን እንደ ሙሽራ አድርጎ ሲወስዳት ልትመለከቱት ትችላላችሁ? ጌታዬ ግን አይወስዳትም። ያ… ያንን ማየት ይከብደኛል። አይ። አስታውሱ፡ አሁን፡ አንድ ወንድና ሚስቱ አንድ ናቸው። እራስህን ከእንደዚህ አይነት ሰው ጋር መቀላቀል ትፈልጋለህ? የምትፈልግ ከሆነ፡ በአንተ ላይ ያለኝን እምነት በእርግጠኝነት ያጠራጥረኛል።

82 ከዚያም፡ እግዚአብሔር ራሱን፡ ከእንደዚህ አይነት፡ ቋሚ ከሃይማኖት ተቋም ሴተኛ አዳሪ ጋር ስለመቀላቀልስ? "የአምልኮ መልክ ቢኖረውም ኃይሉን የሚክድ፡" ይህን የሚያደርግ ይመስልሃል? ፈጽሞ እንዲህ እያደርግም። በውስጧ የእርሱ ባህሪ ሊኖራት ይገባል። እውነተኛዋ፡ በትክክል፡ ዳግመኛ-የተወለደች ቤተክርስቲያን በ—በክርስቶስ የነበረው ባህሪ ሊኖራት ይገባል፡ ምክንያቱም ባልና ሚስት አንድ ናቸውና። ኢየሱስ እግዚአብሔርን የሚያስደስት ነገር ብቻ ያደርግ ከነበረ፡ ቃሉን ጠብቆ ቃሉን ከገለጠ፡ ሙሽራውም ተመሳሳይ ባሕርይ ሊኖራት ይገባል። በምንም መልኩ፡ የሃይማኖት ተቋም፡ መሆን አትችልም። ምክንያቱም፡ ያኔ፡ ምንም ያህል፡ "አይሆንም" ለማለት ብትፈልጉም ምን ማድረግ እንዳለባትና ምን ማድረግ እንደማትችል በሚነግራት፡ ብዙ ጊዜ፡ ከእውነተኛው ቃል፡ ብዙ ማይሎችን በራቀ፡ በቦርድ አባላት ቁጥጥር ሥር ትገኛለች።

83 እግዚአብሔር ቤተክርስቲያኗን ለመምራት ትቶን ከሄደው እውነተኛ መሪ ማምለጣችን በጣም ያሳዝናል። የመንግስት ፕሬስቢተሮችን ልኮ አያውቅም። ኤጲስ ቆጶሳትን፡ ካርዲናሎችን፡ ቀሳውስትን፡ ሊቃነ ጳጳሳትን ልኮ አያውቅም። ቤተክርስቲያኗን ለመምራት፡ መንፈስ ቅዱስን ለቤተ ክርስቲያን ላከላት። "እርሱ መንፈስ ቅዱስ ሲመጣ፡ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፡ የነገርኳችሁን፡ እነዚህን ነገሮች ይገልጥላችኋል፡ ያስታውሳችኋል፡ የሚመጣውንም ነገር ያሳችኋል።" መንፈስ ቅዱስ ይህን ለማድረግ ነው። አሁን፡ ዘመናዊው ቤተክርስቲያን ይህን ትጠላለች። እትወድም፡ ታዲያ የክርስቶስ ሙሽራ መሆን የምትችለው እንዴት ነው? በዛሬው ጊዜ ያሉ ሰዎች ዘመናዊ ሃይማኖት ተቋምን እየመረጡ ነው። ምን ያደርጋል፡ ይህ የሚያሳየው የቃሉን ደካማ ግንዛቤያቸውን ብቻ ነው።

84 ሊጎዳችሁ አይደለም ይህን የምናገረው፡ እስኪታያችሁ ድረስ በውስጣችህ እንዲገባ ነው የምናገረው።

85 ብዙ ጥንዶችን አጋብቻለሁ፡ ነገር ግን ሁልጊዜ ክርስቶስን እና ሙሽራውን ያስታውሰኛል። ከተወሰነ ጊዜ በፊት፡ እዚህ ካደረኳቸው ሠርጎች መካከል አንዱ፡ በ—በሕይወቴ ውስጥ በጣም አስደናቂ ነገር ነበር። ገና ወጣት አገልጋይ ሳለሁ፡ ከብዙ አመታት በፊት ነበር።

86 ወንድሜ በፓዋ እ—እየሰራ ነበር። እንደኔ ያረጀ ሰው ካለ፡ ያስታውስ ይሁን፡ አይሁን፡ አላውቅም። ያ መንግሥት ያ—ያወጣው ፕሮጀክት ነበር። ወንድሜም ሠላሳ ማይል ያህል፡ ሰርቷል። አንዳንድ ሀይቆችን እየቆፈሩ ነበር፡ የጥበቃ ፕሮጀክት ነበር።

87 ከኢንዲያናፖሊስ የመጣ፡ አንድ ልጅ አብሮት ይሠራ ነበር፡ ኦህ፡ ከምኖርበት፡ ወይም ከኖርኩበት፡ ከጄፈርሰንቪል፡ ከ—ከመቶ ኪሎ ሜትር በላይ ነው። እ… አንድ ቀን፡ ለወንድሜ፡ እንዲህ አለው፡ "ዶክ፡" እንዲህ አለው፡ "ለ—ለሰባኪው የ… የምከፍለው በቂ ገንዘብ ቢኖረኝ፡ አገባለው" አለ። እንዲህ አለው፡ "ፈቃድ ለ—ለማውጣት በቂ ገንዘብ አለኝ፡ ግን፡" አለው፡ "ሰባኪውን ለመክፈል ግን በቂ ገንዘብ የለኝም" አለው።

88 ዶክ እንዲህ አለው፡ "ችግር የለውም፡ ወንድሜ'ኮ ሰባኪ ነው፡ እ—እና—ሊያጋባችሁ ይችላል።" እንዲህ አለው፡ "እንዲህ ላለ ነገር ከሰዎች ገንዘብ ተቀብሎ አያውቅም።"

እርሱም አለው፡ "ሊያጋባኝ ፈቃደኛ የሚሆን ከሆነ ትጠይቅልኛለህ? "

89 እና፡ የዛን ምሽት ወንድሜ እኔን ጠየቀኝ። እኔም፡ "ከእነርሱ አንዱንም፡ ኪዚህ በፊት ያላገባ ከሆነ፡ ሁሉ መልካም… አጋባዋለው" አልኩት።

እርሱም፡ "ደህና፡ እዎ፡ እጠይቀዋለው" አለ።

እኔም፡ "ከዚህ በፊት ያላገባ ከሆነ፡ እዚህ እንድመጣ፡ ንገረው" አልኩት።

90 ስለዚህ፡ ቅዳሜ ሰደርስ ልጁ መጣ። ይህንን ሁልጊዜ ወደ ኋላ መለስ ብዬ ማየቴ፡ ለእኔ ትልቅ ነገር ነው። በ… ዝናባማው ከሰአት በኋላ፡ ባረጀ ቼቭሮሌት መኪና፡ የፊት መብራቶች በገመድ ታስረው፡ እየገሰገሰ መጥቶ፡ ፊት ለፊቴ አቆመ። ባለቤቴን በሞት ካጣሁ ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡ ሁለት ትናንሽ ክፍሎችን፡ እየሰራሁ ነበር። ዶክም እ—እነርሱን እየጠበቀ፡ ከእኔ ጋር ነበር።

91 ልጁም—ከመኪና ወጣ፡ በእርጠኛነት ልጁ ለእኔ፡ ሙሽራ አይመስልም፡ ለእኔ ሆነ ለማንም አይመስልም፡ ብዬ እገምታለው። አዎን። በአንድ ዶላር ከግማሽ ጥሩ ጫማ፡ መግዛት እችላለሁ። ያደረገው ጫማ፡ የተንጋደደ ነበር። ሱሪውም በጣም ሰፊ ነበር። ያረጀ የሞለስኪን ጃኬቶች አንዱን አድርጓል። አንዳንዶቻችሁ ትልልቅ ሰዎች ታስታውሳላችሁ ብዬ አላስብም። በደንብ ሳይጸዳ ማጠብያ ማሽን ውስጥ ገብቶ የወጣ ይመስላል፡ መንችኮ ነበር፡ **እንደዚህ፡** ጫፉ ወደላይ ብሎ ተጨራምቶ ነበር።

92 እ—አንዲት ምስኪን ሴትም ከጎን ወጣች፡ ከትንሽ፡ ኦህ፡ ትንሽ የዳማ ቅርጾች—የሚመስል ቀሚስ ለብሳ ነበር።

93 አላውቅም። አንድ ጊዜ፡ እንደዚህ አይነት ነገር ሰጠራ ተሳሰችያለው። ጂንግሃም፡ የሚባል ይመስለኛል። ስለዚህ... [ጉባኤው ሳቀ—እርታዒ።] እንደገና ተሳሰቻለሁ። ሁ—ሁልጊዜም እሳሳታለው። እኔም...

94 ከመኪናው ወረደችና፡ ደረጃውን ወጡ። ሲ—ሲገቡም፡ ምስኪን ትንሽ ነገር፡ እ... እንደምገምተው፡ እሷ፡ የለበሰችው ቀሚስ ብቻ ነበር። እሷም ጫማ፡ አልነበራትም፡ ማለት ይቻላል። ከኢንዲያናፖሊስ፡ እጅ በማሳየት መኪና አስቁማ ነው የመጣችው። ጸጉሯ በረጅሙ፡ እንደ ሹሩባ ተሰርቶ፡ በጀርባዋ፡ ወርዷል። በጣም ወጣት ትመስላለች።

እና እንዲህ አልኳት፡ “ለማግባት እድሜሽ ደርሷልን” አልኳት?

95 እርሷም፡ “አዎ፡ ወዳጄ” አለች። እርሷም፡ “ከአባቴ እና ከእናቴ የጽሁፍ ፈቃድ አለኝ” አለች። እንዲህ አለች፡ “ፊቃድ ለመውሰድ፡ ለፍርድ ቤት—ማሳየት አለብኝ” አለች።

96 እኔም፡ “መልካም፡” እንዲህ አልኳት፡ “ይህን ጋብቻ ከማድረጋችን በፊት ትንሽ ላወራችሁ እፈልጋለው” አልኳት። ቁጭ አሉ። ልጁ ክፍሉን ማየቱን ቀጥሏል፡ ጸጉሩን በጣም መቆረጥ ነበረበት። ክፍሉንም ማየት ቀጠለ። እኔን እየሰማኝ አልነበረም። እኔም፡ “ልጄ፡ የምናገረውን እንድትሰማ እፈልጋለው” አልኩት።

እርሱን፡ “ እሺ፡ ጌታዬ” አለ።

እኔም፡ “ይችን ልጅ ትወዳታለህ” አልኩት?

እርሱም፡ “አዎ፡ ወዳጄ። እወዳታለው” አለ።

እኔም፡ “አንችስ ትወጅዋለሽ” አልኳት?

“አዎ፡ ወዳጄ። እወደዋለው።”

97 እኔም፡ “አሁን፡ ካገባሃት በኋላ የምትወስዳትን ቦታ ኣዘጋጅተሃል? ” አልኩት

እርሱም፡ “አዎ፡ ወዳጄ” አለ።

98 እኔም፡ “መልካም። አሁን።” እንዲህ አልኩት፡ “የሆነ ነገር መጠየቅ እፈልጋለው። እዚህ PWA ፕሮጀችት ላይ እየሰራ እንደሆነ፡ እረዳለው” አልኩት።

እርሱም፡ “አዎ፡ ወዳጄ” አለ። ያ በሳምንት አስራ ሁለት ዶላር ነው።

እኔም “እሷን የሚያኖራት እሰራለሁ ብለህ ታስባለህን፡” አልኩት?

እርሱም፡ “ማድረግ የሚችለውን ሁሉ አደርጋለው” አለ።

99 እኔም፡ “መልካም፡ ያ መልካም ነው” አልኩት። እኔም አልኳት፡ “አሁን፡ ከሰራው ቢወጣስ... ስራውን ቢለቅስ፡ እህቴ? ምን ታደርጊያለሽ፡ ወደ እናትሽ፡ ወደ አባትሽ ቤት፡ ትመለሻለሽን? ” አልኳት

እርሷም፡ “አይ፡ ወዳጄ። ከእርሱ ጋር እቆያለው” አለችኝ።

100 እኔም፡ “አንተስ፡ ወዳጄ፡ ሶስት ወይም አራት ልጆች ሲኖሩህ፡ የሚታበላቸው ነገር ቢጠፋና፡ ምንም ስራ ባይኖርህ። ምን ታደርጋለህ፡ እርሷን ታስናብታታለህን? ”

101 እንዲህ አለኝ “አይ፡ ወዳጄ። እታገላለሁ። በሆነ መንገድ፡ እናሳካዋለን፡” አለኝ።

102 ትንሽ አዘንኩለት። በእውነት እንደሚወዳትና፡ እርስ በርሳቸው እንደሚዋደዱ አየሁ። አጋባኋቸው።

103 የት ወሰዷት ይሆን አሳብ ገባብኝ። ከትንሽ ቀናት በኋላ፡ የት እንዳለ፡ ወንድሜ፡ ዶክን ጠየኩት። እርሱም፡ “ወደ ኒው አልባንይ ሂድ” አለኝ፡ ከእኛ በታች ያለው ትንሹ ከተማ ነው።

104 ቆርቆሮ ጠጋኝ በነበርኩ ጊዜ––ጥቂት ቆርቆሮዎቼ ወደ ነበሩባት፡ ዘወትር የሚሄድባትን፡ ወንዝ ዳር ወደ ነበረች ቦታ ሄድኩኝ። ሌሎች ባልደረቦቼ፡ በዙሪያ ተቀምጠው፡ ሲቀልዱ እና ሌሎች ነገሮችን ሲያደርጉ፡ በዚያ ሰዓት መኪና ውስጥ ገብቼ ወደ ወንዙ እሄድና፡ እጸልያለው፡ ያረጀ ብረት በሚሠራበት ትልቅ ቆርቆሮ ሥር ሆኜ፡ መጽሐፍ ቅዱሴን አነባለው። በዚያም ያረጁ የባቡር ፉርጎዎች ነበሩ።

105 እናም ይህ ልጅ ወደዚያ ሄዴና ከፉርጎዎቹ አንዱን ወሰደና በር ገጠመለት። ጋዜጣና ስፒል ወሰደ።

106 ስፒል ምን እንደሆነ ሰንቶቻችሁ ታውቃላችሁ? እንግዲያውስ፡ ከንታኪያውያን እዚህ የሎም ማለት ነው። እንዲህ ነው፡ የካርቶን ቁራጭ ላይ፡ የምትሰካ፡ ትንሽ መርፌ ናት። ከዚያ እዚያው ላይ ትሰካለች... ስፒል ማለት ያ ነው።

107 ስለዚህ፡ በየቦታው ሰካክተውት ነበር። ወደ ብረት ሥራዎች ሄዶ አንዳንድ ነገሮችን አመጣ፡ እና ወደ ላይ ለመውጣት፡ ደረጃ አደረገ። አንዳንድ ሳጥኖችን ሳጥኖችን አመጣ፡ ጠረጴዛም ለራሱ አመጣ። አንድ ቀን፡ “ወርጄ እንዴት እንደሆኑ እያለው፡” ብዬ አሰብኩ።

108 ከዚያ ከስድስት ወር ቀደም ብሎ፡ የኢ. ቪ. ናይትን ልጅ ከኢ. ቲ. ስላይደር ልጅ ጋር አጋብቼ ነበር። በኦሃዮ ወንዝ ላይ ከሚገኙት እጅግ ሀብታም ሰዎች መካከል አንዱ የሆነው፡ ኢ. ቪ. ናይት፡ ኦህ፡ እዚያ የሚገኘውን ታላቅ ፋብሪካ፡ የፋብሪካ ቤቶችንና፡ ሌሎች ነገሮችን፡ እየሰራ ፋብሪካውን ያስተዳድራል። ስ–– ስላይደር፡ ኢ. ቲ. ስላይደር፡ የአሸዋ እና የጠጠር ኩባንያ፡ የሚሊየነር ልጅ ነው። እኔም አጋባኋቸው።

109 ወደ ቦታ ተመለስኩ፡ ወደ አንድ ጐጆ በመመለስ በትራስ ላይ መንበርከክን፡ ለሁለት ሳምንታት ያህል ተለማመድኩ። ያንን ጥንዶችን ለማጋባት፡ ከመቼውም ጊዜ ካደረግኳቸው ሌሎች ሠርጎች ሁሉ የሚበልጡ፡ ብዙ የተራቀቁና፡ የቅንጦት ዝግጅቶችን ማከናወን ነበረብኝ! እነርሱም፡ በወጡበት ጊዜ፡ እነርሱ... ሌላኛዎቹ ምስኪን ጥንዶች ትንሽ ሶፋ እና ታጣፊ አልጋ ባለበት ትንሽ ያረጀ ክፍል ውስጥ ቆመው ነበር፡ ሁለቱም የተጋቡት ግን በተመሳሳይ ስነ ሥርዓት ነው።

110 ከዚያም፡ አንድ ቀን፡ ወደዚህ ሀብታም ባልና ሚስት ለመሄድ አሰብኩ። ምንም መሰራት አይጠበቅባቸውም፡ አባቶቻቸው ሚሊየነሮች ስለሆኑ፡ ጥሩ ቤት ገንብተውላቸዋል። እውነቱን ለመናገር፡ እዚህ ኮረብታ ላይ የሚገኘው፡ ኢ. ቪ. ናይት፡ በትልቁ ቤቱ ላይ ያሉ የበር መክፈቻዎች የተሰሩት ከአሥራ

አራት ካራት ወርቅ ነው፡ ስለዚህ በምን አይነት ቤት ላይ እንደሚኖር ማሰብ ትችላላችሁ። መስራት የለባቸውም። በየአመቱ ቅንጡ ካዲላክ ይሰጣቸዋል። ልክ፡ እንደ ብቸኛ ልጆች፡ የሚፈልጉትን ሁሉ ያገኛሉ። አንድ ቀን ሰወጣ...

111 አሁን፡ እንዴት ነው ከእነርሱ ጋር የተዋወኩት፡ ከጓደኞቻቸው አንዱ ጥሩ ጓደኛዬ ነው። ሁላችንም ጓደኛሞች ነበርን። በዚህ መንገድ ነው፡ እንዳጋባቸው ስፈልጉኝ የተዋወቅነው።

112 ስለዚህ እነሱን ለመጠየቅ ሄድኩ። አሮጌውን ፎርዴን፡ ውጪ አቁሜ፡ ደረጃዎቹን ወጣሁ። ወ—ወደ ላይ ወጥቼ፡ ትንሽ እንደተቃረብኩ፡ ሰያወሩ ሰማኋቸው። እነርሱም በእርግጠኝነት ሲጨቃጨቁ ነበር። እርስ በርሳቸው ይቀኑ ነበር። ሲደንሱ ነበሩ። እሷ በጣም ቆንጆ ነች። ከእነዚህ ከውበት ንግስቶች አንዷ ነበረች። የውበት ንግስት ሰለሆነች፡ ብዙ ሽልማቶችን ወሰዳለች፡ አንዳድንድ መኪናዎችን እና ሌሎች ነገሮችን አሸንፋለች። ተመለከትኳቸው፡ እሱ በዚህ ጥግ እሷ በዚያ ጥግ ተቀምጠው፡ አብሯት ሰለጨፈረው ልጅ፡ ወይም ሴት፡ ወይም ሰለሌላ ነገር ይጨቃጨቃሉ።

113 እኔ ሰመጣ፡ በፍጥነት ብድግ አሉና እርሰበርሰ ተያይዘው፡ እጅ ለ—ለእጅ ተያይዘው፡ በወለሉ፡ ወደ በር መጡ። እንዲህ አሉ፡ "ወዬ፡ ሰላም፡ ወንድም ብራንሃም! እንዴት ነህ? "

እኔም፡ "ደህና ነኝ። ደህና ናችሁ? " አልኳቸው

114 እና፡ "oh፡" እርሱ እንዲህ አለ፡ "እ—እ... በጣም ደሰተኞች ነን። አይደለንም እንዴ፡ ማር? "

እርሷም፡ "አዎ፡ ውዴ" አለች። አያችሁ?

115 አሁን፡ አያችሁ፡ እውነት ያልሆነ ነገር ነገር እየሆናችሁ ነው። አሁን፡ በተቀባ እሳት መሞቅ አትችሉም፡ ልክ ከእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት መካከል አንዳንዶቹ፡ ከአንድ ሺህ ዓመት በፊት ወይም ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት የሆነውን ጴንጤቆሰጤን ለመሳል እንደሚሞክሩት። በተቀባ እሳት መሞቅ አትችሉም። ጴንጤቆሰጤ በዚያን ጊዜ እንደነበረው ሁሉ ዛሬም እውን ነው። አያችሁ? አዎን። እሳቱ አሁንም እየወደቀ ነው። የተሳለ እሳት አይደለም። እውነተኛ እሳት ነው።

116 ስለዚህ፡ እነሱ፡ በዚያው ነበሩ። አየህ? እ—እንደዚያ መኖር አልፈልግም.

117 "ኡህ፡" እንዲህ አሰብኩ፡ "ታውቃላችሁ፡ እዚያ ኮረብታው አጠገብ ወንዙ ጋር፡ ሌሎች ጥሩ አጨራረሰ ያልነበራቸው ጥንዶች ነበሩ።" "አንድ ቅዳሜ ከሰዓት ወደዛ እወርድና እንዴት እንደሆኑ አያችኋለው፡" ብዬ አሰብኩ።

118 ሰለዚህ እኔ፡ በፊቴ ቆሻሻ ነበር፡ መሳሪያ ይዤ፡ ሁሉም ነገሬ ቆሸሾ ነበር። "ሄጄ እነርሱን አያቸዋለው፡" ብዬ አሰብኩ። ከሰልክ ሽቦው ጎን ለጎን፡ በወንዙ ዳር የኤሌክትሪክ ገመዶች አጠገብ ሴሄድ፡ መብረቅ ወይም በሌላ ነገር የተሰነጠቁ ኢንሱሌተሮች ሰላሉ፡ በጥንቃቄ ነው የሄድኩት። አሮጌው ቼቭሮሌት መኪና፡ ከፊት ለፊት ቆሞ ነበር። ካገባኋቸው ከአንድ አመት፡ ገደማ በኋላ ነው። እና እንዲህ ነበር—በ... በሩ ክፍት ሰለ ነበረ፡ ሲናገሩ እሰማቸው ነበር። ይህ ግብዝነት ሊመሰል ይችላል፡ ነገር ግን ምን እንደሚናገሩ መሰማት እሰከምችል

ድረስ፡ ምን እንደሚናገሩ ለመስማት ተጠጋኋቸው። እዚያው ቆምኩ። ለራሴ ብቻ ማወቅ፡ ፈልጌ ነው።

119 የማወራውን ነገር እንደማውቅ እርግጠኛ መሆንና ማወቅ እፈልጋለሁ። ስለ እግዚአብሔር ቃል የማደርገው በዚህ መንገድ ነው። እውነት ነው፡ ወይስ አይደለም? ቃሉን ይጠብቃል፡ ወይስ ቃሉን አይጠብቅም? ቃሉን የማይጠብቅ ከሆነ፡ እንግዲያውስ እርሱ እግዚአብሔር አይደለም። አያችሁ? ቃሉን ከጠበቀ፡ እግዚአብሔር ነው። አያችሁ?

120 እንዴት እንደሚሆኑ ለማየት ፈለግኩ። በጣም በቀላሉ፡ ወደ ጎን ጠጋ አልኩ። እንዲህ ሲል ሰማሁት፡ "ኦህ፡ የኔ ማር፡ ያንን እንድገዛልሽ፡ በጣም ፈልጌ ነበር።"

121 እርሷም፡ "አሁን፡ አየህ፡ ውዴ" አለች። "ይህ ልብስ ቆንጆ ነው፡" አለችው። እንዲህ አለች፡ "ለምን፡ ይህ በቃ ጥሩ ነው" አለች። አለችም፡ "አመሰግናለሁ። ግን አየህ... "

122 በባቡሩ ፉርጎ ላይ ያለው በር በደምብ ስላልተዘጋ፡ በቀዳዳው ለማየት ብዬ፡ ቀስ ብዬ ተጠጋሁ። እዚያ ውስጥ፡ ተቀምጦ፡ እሷ በጭኑ ላይ ተቀምጣለች፡ እና እርስ በርስ፡ ተቃቅፈዋል። እና ከድሮ ባርኔጣዎች አንዱ አጥልቆ ነበር፡ ትንሽ ቀዳዳ ነበራትና፡ ከላይ፡ ከፈታት፡ ከዚያ ውስጥ፡ የክፊያ ቼክ አወጣ። አውጥቶ በጠረጴዛው ላይ አደረገ። እንዲህ አለ፡ "ይሄን ያክል ለግሮሰሪ። ይሄን ያክል ለኢንሹራንስ። ይሄን ያክል መኪናው።" ገቢያቸው ወጪውን በሙሉ መሸፈን አልቻለም። እዚያ በመሸጫው መስኮት ላይ፡ አንድ ዶላር ወይም ሌላ የሚያስወጣ፡ ትንሽ ልብስ አይቶ፡ ለሳምንታት እያዬ እንደነበረ አዋስተዋልኩ። ሊገዛላት ፈልጎ ነበር። እንዲህ አለ፡ "እና፡ የኔ ማር፡ በልብሱ በጣም ቆንጆ ትሆኚ ነበር።" እና ሲላት...

123 እርሷም፡ "ነገር ግን፡ ማር፡ ል—ልብስ አለኝ። በ—በእውነት አያስፈልገኝም" አለች። አያችሁ? ያች ምስኪን ንግስት...

124 ወደኋላ ተመለስኩና፡ ወደላይ ተመለከትኩ። በሌላኛው ቤት እናት ላይ የሚገኘውን፡ ግንብ አየሁት። እዚያው ቆሜ፡ ትንሽ ደቂቃ ተመለከትኩ። "ማነው ሃብታም ሰው፡" ብዬ አሰብኩ? "ቢሊ ብራንሃም፡ የሆነ ቦታ ምረጥ ብትባል፡ የት ነበር፡ የምትሄደው፡" ብዬ አሰብኩ? ለእኔ፡ ያንን በኮረብታው እናት ላይ ያለውን የሚያምረውን ነገር አልመርጥም። እንደ እውነተኛ የቤት እመቤት፡ እዚህ ታች ያለውን ይህንን ገጸ ባህርይ እመርጣለሁ፡ የምትወደኝንና ከእኔ ጋር የምትኖር፡ ቤቱን ቤት ለማድረግ የምትሞክረውን፡ ለጌጣ ጌጥ፡ ወጪ የማታስወጣ፡ ከአንተ ጋር የምትኖር፡ አካልህ የሆነች እመርጣለሁ።

125 ያ እንዴት መሆን እንዳለበት፡ ዘወትር በውስጤ አለ። አንደኛው ቆንጆ ልጅ መረጠ፡ ሌላኛው ደግሞ ባህርይን መረጠ። አሁን፡ ያ መምረጥ የሚትችሉበት ብቸኛው መንገድ ነው። በመጀመሪያ፡ ባህርይ ተመልከቱ፡ ከዚያም፡ የሚትወዳት ከሆነ፡ ጥሩ ነው።

126 አስተውሉ፡ የእግዚአብሔር የመጀመሪያው አዳም፡ ሚስቱን ለመምረጥ ዕድል አልነበረውም። አማራጭ አላገኘም። እግዚአብሔር አንድ አድርጎ ፈጥሮታልና፡ ሊመርጣት አልቻለም ነበር። ስለዚህ እርሷ ከእግዚአንሔር ቃል ውጪ እንደመራችው እናውቃለን። ስለ ጉዳዩ መጸለይ አልተቻለውም። እሱ—

እንደ እኔና እንደ እናንተ አ—አይደለም። ሌላ አማራጭ አልነበረውም። ከዚህም በተጨማሪ፡ ይህን በማድረጓ የእግዚአብሔር ልጅ ከመሆን ትክክለኛ ቦታውን አሳጣችው። ይህንንም ያደረገችው ይበልጥ ዘመናዊ የሆነ የአኗኗር ዘይቤ በማሳየት፡ ማድረግ የሌለባቸውን ነገር በማድረግ ነው። ነገር ግን ባህሪዋ እሷ እንደተሳሳተች አሳይቷል። ምክንያቷም ሆነ ዓላማዋ የተሳሳተ ነበር። በንግግሯም፡ አሳመነችው፡ ያገኘችው አዲስ ዘመናዊ ብርሃን፡ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚቃረን፡ የተሻለ የአኗኗር ዘይቤ ነበር።

127 ዛሬም ሰንት ሴቶች፡ ወንዶችን፡ ወንዶችም መልካም ሴትን፡ ከእግዚአብሔር ያሰወጧቸው ይሆን፡ ወይም መልካም ወንዶችን ከእግዚአብሔር ሊያርቁ ይችሉ ይሆን፡ እንዲህ እያሉ፡ "ይህ ሃይማኖት፡ እናንተ የጴንጤቆስጤ ልጆች፡ ያ ሃይማኖት፡" "ኡህ፡ ያ ኋላ-ቀር ፋሽን ነው፡ ያረጀ ጭጋግ ነው፡ ያንን አትመን፡" ይላሉ። ያቺን ልጅ ከማግባትህ በፊት አጥብቀህ ብትጸልይ ይሻልሃል፡ የቱንም ያህል ቈንጆ ብትሆን ግድ የለኝም። ለወንዶችም ተመሳሳይ ነገር ነው።

128 ከእግዚአብሔር ፍቃድ ውጪ አወጣችው እና ማድረግ የሌለበትን ነገር እንዲያደርግ አደረገችው፡ ያም፡ ለሰው ልጅ ዘር ሁሉ፡ ሞትን አስከተለ። ለዚያም ነው መጽሐፍ ቅዱስ እንድታስተምር፡ ወይም እንድትሰብክ፡ ወይም የእግዚአብሔርን ቃል በምንም መንገድ፡ እንዳታስተናግድ የሚከለክላት።

129 እኅቶች፡ ብዙዎቻችሁ፡ "ጌታ ለመሰበክ ጠርቶኛል፡" እንደምትሉ አውቃለሁ።

130 ከእናንተ ጋር አልጨቃጨቅም። ነገር ግን እነግራችኋለው፡ ቃሉ አታድርጉት ይላችኋል። "አታስተምር፡ ወይም አትሰልጥን፡ ነገር ግን ዝም ትበል።"

"እሺ፡" እንዲህ ትላላችሁ፡ "ጌታ ያንን አድርጊ ብሎኛል።"

131 ያንን ምንም አልጠራጠረውም። በቀደም ማታ ሰለ በልዓም የሰበኩትን ሰምታችኋል? በለዓም የመጀመሪያውን፡ ቀ-ቀጥተኛ የእግዚአብሔርን ውሳኔ ተሰጠው። "አታድርግ።" ነገር ግን በመጨረሻም እግዚአብሔር ሄዶ እንዲያደርገው እስኪነግረው ድረስ በተነገረው ትዕዛዝ አልጸናም።

132 እግዚአብሔር እንድትሰብኪ ይፈቅድልሽ ይሆናል። አይፈቅድም አልልም። ነገር ግን እንደ መጀመሪያው ቃል እና እቅዱ አይደለም። "ሕግ ደግሞ እንደሚል፡ ትገዛ።" እውነት ነው። ስለዚህ፡ ማድረግ የለባትም።

133 አሁን ደግሞ፡ የተፈጥሮ ሙሽራ እንዴት የመንፈሳዊውን ተምሳሌት እንደሚሆን አስተውሉ። ቃሉ ሲናገር፡ እንዲህ ይላል፡ "ሴት ለወንድ ተፈጠረች እንጂ፡ ወንድ ስለ ሴት አልተፈጠረም።"

134 አሁን፡ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ፡ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሙሽራ፡ እናገራለሁ፡ ነገር ግን ዳራውን ላሳያችሁ እየሞከርኩ ነው።

135 "ሴት ለወንድ ተፈጥራለች፡ ወንድ ለሴት አይደለም።" ለዛ ነው፡ በቀድሞ ህግ መሰረት፡ ከአንድ በላይ ማግባት ህጋዊ የሆነው። ዳዊት ከአምስት መቶ ሚስቶች ጋር በዚያ ተቀምጦ ተመልከቱት፡ መጽሐፍ ቅዱስም ሲናገር፡ "እንደ እግዚአብሔር ልብ ያለ ሰው ነበር።" ከአምስት መቶ ሚስቶች ጋር፡ ሰሎሞንም

ከአንድ ሺህ ጋር፡ ነገር ግን ከሴቶች ውስጥ አንዳቸው እንኳን ሌላ ባል የላቸውም።

136 **ጋብቻ እና ፍቺ** በሚለው ርዕስ የሰበኩትን የቴን ካሴት ታገኛላችሁ። ያ፡ እዚህ በቅርብ ጊዜ፡ በቱክሰን ተራራ ላይ፡ ሰለሱ እየጸለይኩ ነበርኩ። የእሳት አምድ ተራራውን ሲዞርና፡ ወደ ኋላ እና ወደ ፊት ወደ ላይ እና ወደ ታች፡ ሲሄድ ለመመልከት፡ ትምህርት ቤቶችን አቋረጡ። በዚህ ዙሪያ ያሉ ሰዎች ያውቁታል፡ እዚያም፡ አይተውታል። እና... የዚህን የጋብቻ እና የፍቺ ጥያቄዎች እውነት ሲነግረኝ። አንዱ **በዚህ** አቅጣጫ የሚሄድ ከሆነ፡ ሌላኛው ደግሞ **በዚያ** አቅጣጫ የሚሄድ ከሆነ፡ የሆነ ቦታ እውነት መኖር አለበት። ከእነዛ ሰባቱ ማህተማት በኋላ፡ እውነቱ ምን እንደሆነ አሳየኝ።

137 አሁን፡ አስተውሉ፡ አንድ ባል እንጂ ከዚያ በላይ ሊኖራት አይችልም፡ ምክንያቱም፡ "ሴት የተፈጠረችው ለወንድ ነው እንጂ፡ ወንድ ለሴት አይደለም።" እነዛ ሁሉ አምስት መቶ ሴቶች የዳዊት ሚስቶች ብቻ ነበሩ፡ ያም ምሳሌ ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ በሚሊኒየም ዙፋን ላይ ሲቀመጥ፡ ሙሽራይቱ አንድ ሰው ብቻ አትሆንም፡ ነገር ግን አስር ሺዎች፡ ሙሽሮች፡ ሁሉም በአንዴ ይመጣሉ። ዳዊት እንደ ግለሰብ፡ ብዙ ሚስቶች ነበሩት፡ ነገር ግን ሁሉም በአንድነት ሚስቶቹ ነበሩ። የአማኞች ሙሉ አካል የክርስቶስ ሙሽራ እንደሆነ፡ ምክንያቱም እሷ ሴት ናት፡ እርሱ ወንድ ስለሆነ። ማለት፡ ለክርስቶስ የተፈጠርነው እኛ ነን። ክርስቶስ ለኛ አልተፈጠረም።

138 በዛሬው ጊዜ በመማሪያ መጽሐፋችን ውስጥ የምናደርገው ይህንኑ ነው፡ ቃሉን (ማለትም ክርስቶስን) ለእኛ እንዲስማማ ለማድረግ መሞከር ነው፡ ራሳችን ከቃሉ ጋር ለማስማማት ከመሞከር ይልቅ። ያ የተለያየ ነበር ነው።

139 አንድ ወንድ ከአንድ ቤተሰብ አንዲትን ሴት ሲመርጥ፡ በውበት ላይ መደገፍ የለበትም፡ ውበት እታላይ ነውና። ውበትም፡ የአሁን የዓለም ውበት፡ ከዲያቢሎስ ነው።

"ኦህ፡" አንድ ሰው እንዲህ ሲል እሰማለሁ፡ "እዚህ ጋር ተጠንቀቅ፡ ሰባኪው!"

140 በዚህ ዓለም ላይ ያሉ ነገሮች ሁሉ፡ ውብ ተብሎ የሚጠሩት፡ ፈጽሞ ከዲያብሎስ ናቸው እላለሁ። አረጋግጥላችኋለሁ። ከዚያም፡ በዚህ አባባል መሰረት፡ ትክክል መሆኑን አለመሆኑን፡ በቅዱሱ በእግዚአብሔር ቃል እንፈልግ። አንዳንድ ሴቶች በጣም ቆንጆ መሆን ትፈልጋላችሁ! ከየት እንደመጣ ተመልከቱ። በመጀመሪያ፡ ሰይጣን መላእክትን እስኪያስት ድረስ በጣም ቆንጆ ሆኖ እናገኘዋለን። ደግሞም ከሁላቸውም እጅግ ውብ መልአክ እርሱ ነበር። ውበት በዲያብሎስ እንደሆነ፡ አሳይቷል። ምሳሌ ሲናገር፡ ሰለሞን ሲናገር፡ "ውበት ከንቱ ነው፡" ብሏል። ያ ትክክል ነው። ሀጢአት ውብ ነው። በእርግጠኝነት። ማራኪ ነው።

141 አንድ ነገር ልጠይቃችሁና፡ የሆነ ነገር ልነግራችሁ እወዳለሁ። በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ፡ እንድታስተውሉ እፈልጋለሁ። በምድር ላይ ካሉ ዘሮች ሁሉ፡ ከወፎች፡ ከእንስሳት፡ በእንስሳት ህይወት፡ ከሰው ልጅ በስተቀር፡ ቆንጆው ወንድ እንጂ፡ ሴቷ እንዳልሆነች እናገኛለን። ያ ለምን? አጋዘኑን ተ... ተመልከቱ፡ የ—የሚያምር ቀንድ ያለው ተባእት አጋዘን፡ እና ምስኪኗ ሴት

አጋዘን ተመልከቷቸው። ዶሮ—ተመልከቷት፡ ትንሽ፡ ነጠብጣብ ያለባት ዶሮ፡ እንዲሁም ትልቅና ቄንጆ-ላባ ያለውን አውራ ዶሮ ተመልከቱት። ወንዱን ወፍ እና ሴቷን ወፍ ተመልከቷቸው። ወንድ ዳክዬ እና ሴቷን ዳክዬ ተመልከቷቸው። አያችሁ? በዓለም ላይ እንደ ሴት ሊያታልል የሚችል እና ሞራል የሌለው፡ የተፈጠረ፡ አንድም ዝርያ የለም።

142 አሁን፡ እህቴ፡ ተነስተሽ አትሂጂ። የዚህን መጨረሻ እስከምንሰማ ብቻ ጠብቂ። አያችሁ? አያችሁ?

143 ከእንስቶች መካከል ከሴት በቀር፡ ክፉ ስነምግባር ያላት የለችም። ውሻን "ባልጌ፡" አሳማንም፡ "ል—ልክስክስ"ብላችሁ ትጠራላችሁ፡ ነገር ግን፡ ከሞራል አንጻር ሲታይ፡ ከግማሽ ከሚበልጡ ከፊልም አክተሮች የተሻለ ሞራሎች አላቸው። በሥነ ምግባር ከመኖር ውጭ ሌላ ሊሆኑ አይችሉም።

144 ለብልሹነት፡ የተለወጠችው ሴቲቱ ነበረች። ያ ትክክል ነው። ውበቷ ወዴት እንደሚወስዳት አያችሁ? አሁን፡ ለዚያም ነው፡ ዛሬ፡ ሴቶች ውበት እየጨመሩ መሆናቸውን እናውቃለን። ፐርል ብራያንን እንደ ምሳሌ እንውሰድ፡ ፎቶዋን አይታችሁ ታውቃላችሁ? ውበቷ የአሜሪካ ታላቅ ውበት ነው የሚባለው። አሁን ግን በየትኛውም ትምህርት ቤት ካሉ የትምህርት ቤት ኮረዳዎች እሷን ከኋላኛው—ረድፍ የማያታስልፋት ኮረዳ የለችም። እንዲህ መሆን እንዳለበት ታውቃላችሁ? መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ መሆን እንዳለበት እንደሚናገር ታውቃላችሁ?

145 ውድቀቱ ከመጀመሪያው በሴቶች እንደመጣ ታውቃላችሁ? ውድቀት... መጨረሻውም እንደዚሁ ይሆናል፡ ሴቶች ሥልጣን ይይዛሉ በወንዶች ላይ ይገዛሉ፡ ወዘተ። መጽሐፍ ቅዱስ ይህን እንደሚል ታውቃላችሁ? ታውቃላችሁ፡ የወንዶችን ልብሰ ለብሳ፡ ፀጉሯን ስታሳጥር፡ እነዚህ ሁሉ ነገሮች ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚቃረኑ ናቸው። ቤተክርስቲያንንም እንደምትወክል ታውቃላችሁ? ሴቶች የሚያደርጉትን ስትመለከቱ፡ ቤተክርስቲያን ምን እንደምታደርግ ታያላችሁ። ያ በትክክል ትክክል ነው። አሁን፡ አሁን፡ የእግዚአብሔር ቃል እውነት እንደሆነ ሁሉ ይህም እውነት ነው።

146 እንደ ሴት በሞራል ዝቅ ማለት የሚችል ሌላ እንስት አልተፈጠረም። አሁንም፡ በዚህ-... ምክንያት፡

147 በመጀመሪያው ፍጥረት ውስጥ አልነበረችም። ሌሎች እንስቶች በመጀመሪያው ፍጥረት ውስጥ ናቸው፡ ወፎች፡ ወንድና ሴት፡ እንስሳት ሁሉ፡ ወንድ እና ሴት ናቸው። በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ፡ ግን፡ እግዚአብሔር ወንድን ነው የፈጠረው፡ ሴትን ከእርሱ ዘንድ ያወጣት። ሴትም የወንድ ተረፈ-አካሉ ናት፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር እንደዚህ ዓይነት ነገር አልፈጠረም። ቅዱሳት መጻሕፍትን መርምሩ። በትክክል። እግዚአብሔር፡ በመጀመሪያው ፍጥረቱ አልፈጠራትም፡ በጭራሽ፡ ወዳጄ። አልተካተተችም።

148 ይሁን እንጂ ራሷን መግዛት ከቻለች ከወንዶች የበለጠ ሽልማት ታገኛለች። በፈተና ሜዳ ላይ ተቀምጣለችና። በእርሷ በኩል ሞት መጣ። የሁሉም ሞት ተጠያቂ ናት። ነገር ግን እግዚአብሔር ዞር ብሎ ሕይወትን እንደገና ለማምጣት አንድ ሰው ተጠቀመ፣ ታዛዥ የሆነውን፡ ልጁን በሴት በኩል አመጣ። ነገር ግን መጥፎ ሴት—ከሁሉ የከፋች ነች፡ እንደሷ ዝቅተኛ የለም።

149 የሰይጣን ልጅ የነበረው፡ ቃየን፡ እግዚአብሔር ውበትን ይወዳል ብሎ አሰበ። ዛሬም እንደዚያ ያደርጋል። ቃየን የሰይጣን ልጅ ነበር። “ኦህ፡ አሁን!” ትላላችሁ። ስለዚህ ጉዳይ በዝርዝር እንነጋገርም፡ ነገር ግን ላብራራላችሁ እወዳለሁ። መጽሐፍ ቅዱስ እርሱ “ከክፉው” እንደሆነ ይናገራል። ስለዚህ፡ ያ ያረጋግጠዋል። እሺ። አሁን፡ እርሱ የሰይጣን ልጅ ነበር። መሠዊያን ማዘጋጀትና ለዓምልኮ በጣም ቈንጆ ማድረግን፡ እግዚአብሔር ያከብረዋል፡ ብሎ አሰበ።

150 ዛሬም ተመሳሳይ ነገር፡ ያስባሉ። እርግጥ ነው። ይህ፡ “ታላቅ ሕንጻ እንገነባለን። ታላላቅ የሃይማኖት ተቋሞች ይኖሩናል። ትልቅ ሕንጻ እንገነባለንና ምርጥ-ልብስ የለበሱ ሰዎችን፡ በጣም የተማሩ ቀሳውስቶችን እናመጣቸዋለን” ብለው ያስባሉ። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ከዚህ ከአሥር ሚሊዮን ማይልስ ይርቃል። አዎን በትክክል። ሆኖም፡ ቤተ ክርስቲያን ነው።

151 ስለዚህ፡ እግዚአብሔር አምልኮን፡ ቅንነትን፡ መሥዋዕትን የሚያከብር ከሆነ፡ ቃየን ልክ እንደ አቤል ነበር። ነገር ግን ወላጆቹ የበሉት፡ አፕል አለመሆኑን በመገለጥ ተረዳ።

152 እዚህ ላይ አገልጋይ የማይናገረው ነገር እናገራለሁ፡ ግን ለማንኛውም፡ እናገረዋለው። እነዚህ ሌሎች ሰዎች ነገሮችን ሲናገሩ እሰማለሁ፡ እ... ትናንሽ ቀልዶችን ሲናገሩ እሰማለሁ፡ እንደዛ ማለቴ አይደለም። እኔ ግን፡ እንዲህ እላለሁ፡ “አፕል መብላት ሴቶቹ ራቁታቸውን መሆናቸውን እንዲገነዘቡ ካደረገ፡ አፕሉን እንደገና ማደል አለብን።” አያችሁ? አያችሁ? ኡህ-ሁህ። ለዚያ ይቅርታ አድርጉልኝ፡ ግን ያ እንዲለወጥ ብቻ ነው። እዚህ ስለ ሴቶችና፡ የመሳሰሉትን፡ እያወራው አቆየኋችሁ። እ—እ—አሁን ለቀጣዩ ለአንድ ደቅቃ፡ ሪላክስ እንዲታደርጉ እፈልጋለው። አሁን፡ አስተውሉ፡ እ... አፕል አልነበረም። እናውቃለን።

153 ቤተክርስቲያን በእነዚህ ቀናት፡ እንደማንኛውም፡ ሰው-ሠራሽ ሰኬት፡ ሳይንሳዊ እየሆነች ነው። በፎቶ እና በታላላቅ ግምቦች በመሳብ፡ ሳይንሳዊ ቤተ ክርስቲያን ለማድረግ እየሞከሩ ነው። የጴንጤቆስጤውያኑም እንዲህ ዓይነት አኗኗር መከተላቸው በጣም ያሳዝናል። የእግዚአብሔር መንፈስ በዙሪያችሁ ሆኖ፡ በከበሮ እያመለካችሁ፡ ዝቅ ብትሉ ይሻላችኋል። ነገር ግን ከሌሎቹ ጋር ለመወዳደር እየሞከራችሁ ነው፡ ምክንያቱም ተደራጅታችኋል። ያ ነው ያደረገው። አያችሁ? ቤተክርስቲያኖች ሳይንሳዊ ለመሆን እየሞከሩ ነው።

154 አስታውሱ፡ ሰው በሳይንስ እድገት ሲያገኝ፡ በየቀኑ ራሱን እየገደለ ነው። የጠመንጃ ዱቄት ሲፈጥር፡ ምን እንዳደረገ ተመልከቱ። መኪና ሲፈጥር፡ ከጠመንጃ ዱቄት የበለጠ ይገድላል። አሁን ለራሱ ሃይድሮጂን ቦምብ ሰራ። በዛ ምን ሊያደርግ ይሆን? በትክክል።

155 ቤተክርስቲያንም እንዲሁ፡ በሳይንስ በሰው-ሠራሽ እቅድ፡ ለማሳካት ስትሞክር፡ ከእግዚአብሔር እየራቀችና፡ ከመጀመሪያው ይልቅ፡ ወደ ሞት እየወሰደችህ ነው። ትክክል ነው። ሚስትህን በመረጥክበት መንገድ ቤተክርስቲያንም አትመርጥ። አያችሁ? ሳይንስ ለእርሷ ያደረገው ነገር ድንቅ ነበር፡ ነገር ግን በዚህ ጉዳይ ላይ ከቤተክርስቲያናችሁ ብትርቁ ይሻላል፡ ቀለሞችን፡ ዱቄቶችን፡ እነዚህን ሁሉ ሌሎች ነገሮችን ሰርቷል። በቃሉ ባህሪ ምረጥ።

156 አሁን ደግሞ የዛሬዋን ተፈጥሯዊ ሙሽራ ከ-ዛሬዋ የቤተ ክርስቲያን ሙሽራ ጋር እናወዳድር። ዛሬ ልታገባ የምትሄድ፡ ሴትን አስተያዩ።

157 አሁን፡ ሳይንስ ለእሷ ምን እንዳደረገ ተመልከቱ። በመጀመሪያ፡ ፀጉሯን ተቆርጣ፡ እንደ ጃክሊን ኬኔዲ ዓይነት ጸጉር ይዛ፡ ትወጣለች፡ እያችሁ፡ ወይም እንደዛ ያለ ነገር አድርጋ ወጣች። መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚል ታውቃላችሁ? መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ሴት፡ ጸጉሯን የሚታሳጥር ከሆነ፡ አንድ ወንድ ከፈለገ፡ በፍቺ የመፍታት መብት አለው። “ፀጉሯን የምትቆርጥ፡ ክብር የጎደላት ሴት ናት፣” መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ብሏልና። ትክክል ነው። አታውቁትም? ኧሃ? ኦህ፡ እዎ! ይህን እንዲታውቁ በካሊፎርኒያ ውስጥ ብዙ እሰብካለሁ። ትክክል ነው። ኦህ፡ አዎን! እኔ ምን ይጠቅመኛል? እነርሱ እንደፈለጉት፡ ያደርጉታል። አሳማ ወሰዳችሁ ሰሙን ቀይራችሁ፡ በግ ልታደርጉት አትችሉም። አስተውሉ።

158 ከዚህ በኋላ ትጠሉኛላችሁ፡ ግን እውነቱን ታውቁታላችሁ። እያችሁ?

159 ተመልከቱ። እስቲ እናነጻጽረው። እነሆ ከብዙ መኳኳያ ጋር ትመጣለች፡ ያልሆነችው ነገር፡ ዘመናዊ ሙሽራ ትሆናለች። ፊቷን እጠቡት፡ ምናልባት፡ ሊጠፋ ይችላል። ያ የተቀባችውን ሁሉ ሰታነሱ፡ ፍቷ እስከ ሞት ሊያስፈራችሁ ይችላል። እንዲሁም ቤተክርስቲያኗ ትልቅ፡ የተኳኳለ የፊት ገጽታ አላት፡ የተሟላ ሥነ-መለኮታዊ ማክስ ፋክተር አላት። ኧህ-ሃህ። ሁ——ሁለቱም ቄንጆ፡ የውሸት ገጽታ አላቸው፡ ሰው-ሠራሽ ውበት ነው ያላቸው እግዚአብሔር-የሰራው ውበት አይደለም። በሁለቱም ውስጥ ብዙ ባህርይ የለም።

160 አስተውሉ፡ ልክ እንደ ሰይጣን፡ ለማታለል በቂ ነገር አላት፡ ከእሷ ጋር አሁን ዘመናዊ ሙሽራይቱን አወዳድሩ፡ አጫጭር ሱሪዎችን ትለብሳለች፡ መካፕ ትለብሳለች፡ ፀጉሯን ትቆርጣለች፡ እንደ ወንዶች የሚመስሉ ልብሶችን ትለብሳለች፡ ያ ሁሉ ምንም ችግር እንደሌለው የሚነግራትን ፓስተር ትሰማለች። እሱ አታላይ ነው። ከአድማስ ባሻገር ባለው ክልል ይስቃይበታል። በትክክል። ይህን የምታደርገው ለማታለል፡ ያልሆነችውን ነገር ለመምሰል ነው።

161 ቤተ ክርስቲያን የምትሠራው በዚህ መንገድ ነው፡ ትልቅ ዲዲ፡ ፒኤችዲ፡ ኤልኤልዲ አላት። ስለዚህ እንዲህ ትላላችሁ፡ “ፓስተራችን **ይህ**፡ **ያ**፡ እና **ሌላው** ነው” ትላላችሁ፡ ምናልባት አንድ ሆተንቶት ስለ ግብጽ ኃያላን ከሚያውቀው በላይ ስለ እግዚአብሔር አያውቁም። ያ ትክክል ነው። በትክክል። አንዳንድ የሰነ መለኮት ሴሚናሮች እዚያ ይለማመዳሉና፡ ስለ እግዚአብሔር ምንም በላይ አያውቁም።

162 ዘመናዊው ቤተክርስቲያንና የእነርሱ ሥነ መለኮታዊ መካፕ፡ እህም፡ በአንዳንድ አፈ ቀላጤ ፓስተሮቻቸው፡ ልክ እንደ ኤልዛቤል፡ ሴቶቻቸው ሁሉ ክብራቸውን ተላጭተዋል። የቤተ ክርስቲያኒቱ ቁመና፡ በቲኦሎጂካዊ እሳቤ፡ በሜካፖች፡ በአጫጭር ልብሶች፡ እና በጽጉረ ክርክሞች በተቀመሩ ሴቶች የተገነባ ነው። በትክክል። መንፈሳዊ ባህርይዋ በሙሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀበላት ከሚመጣው የቤት እመቤትነት የራቀ ነው።

163 ማንኛውም ክርስቲያን እንዲህ ያለች ሴት ካገባ፡ ከጸጋው እንደወደቀ ያሳያል። እንደዚህ አይነት ሴት ሲመርጥ፡ ለእግዚአብሔር እና ለቤቱ ያለው ጣዕም፡ መሆን ካለበት፡ እጅግ የራቀ ይሆናል። በጭራሽ፡ ወዳጄ። በእርግጥ እሷ ክርስቲያናዊ ጣዕም ያለው አይስማማትም። መንፈሳዊ ባህርይዋ በሃይማኖታዊ

ተቋም ውበት እና ምኞት ጋር በተያያዘ፡ በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያለ፡ የሞተ ነው።

164 ቤተክርስቲያን ዛሬ የቆመችበት ትክክለኛ ቦታ ይህ ነው፡ ለሳይንሳዊ ሰው-ሠራሽ ሃይማኖት፡ በቃል-የተሰጠውን ባሕሪዋን ለሰይጣን ሸጠች። ይህች ቤተ ክርስቲያን፡ የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን በመሆኗ፡ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር እንድትቆይና፡ መንፈስ ቅዱስ በውስጧ እየሰራ፡ አካሏን ከእግዚአብሔር ቃልና ፍቅር ጋር እንዲቀላቀል የማድረግ መብት ነበራት። ይልቁንም፡ እንደ ዔሳው፡ የብኩርና መብቷን ሸጠችና፡ የሃይማኖት ተቋም፡ ተቀበለች፡ ልክ እናቷ ታዋቂ ለመሆን በኒቂያ፡ በሮም እንዳደረገችው፡ የፈለገችውን ሁሉ እንድታደርግ፡ ፈቀዱላት። የእግዚአብሔር ቃል!

165 ኦህ፡ እንዴት ወደ የጴንጤቆስጤ አድማሳችን ውስጥ ገባ! በጣም መጥፎ ነው፡ ነገር ግን ገብቷል።

166 አንድ ደቂቃ ብቻ፡ አስተውሉ፡ በካቶሊክ ቤተክርስቲያን ውስጥ ያለች መነኩሴ። ይህች ሴት፡ መነኩሴ ለመሆንና፡ የመጨረሻውን ምንኩስናን ለመቀበል፡ ሙሉ በሙሉ ለዚያች ቤተክርስቲያን ትሸጣለች። ይህች ሴት (ነፍስ፡ ስጋና፡ መንፈስ) የዚያች ቤተ ክርስቲያን ንብረት ናት። የራሷ አእምሮ የላትም። የመጨረሻውን የምንኩስና ማዕረግ ስትቀበል፡ የራሷ አእምሮ፡ የራሷ ፈቃድ፡ ሊኖራት አይችልም። እዚህ ተመልከቱ፡ ሰይጣንም እንደ እውነተኞቹ፡ አስመሳዮች ያደርጋቸዋል።

167 እውነተኛዋ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን፡ ሙሽራዋ፡ የክርስቶስ አስተሳሰብ በውስጣችሁ እስኪኖር ድረስ፡ ለእርሱና ለተሰፋ ቃሉ የተሸጠች ናት። እንዴት ያለ ልዩነት ነው!

168 እናም ዛሬ ያለችው፡ ዘመናዊው ቤተክርስቲያን፡ ዘመናዊው የዓለም ቤተክርስቲያን፡ ዘመናዊው የዓለም ቤተክርስቲያን እና ደግሞ መንፈሳዊው ቤተክርስቲያን ወንዶች ልጆችን ለመውለድ፡ ሁለቱም ነፍስ ጡር ናቸው።

169 ከነዚህም መካከል፡ አንደኛው፡ የሃይማኖት ተቋም ልደት፡ በ... እነዚህ... ቀናት፡ ውስጥ፡ በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል ውስጥ ይፈጸማል፡ ይህም ለዓለም የክርስቶስ ተቃዋሚን፡ በሃይማኖት ተቋም አማካኝነት ይወልዳል። ይህ በትክክል እውነት ነው። ይህን ለማየት በሕይወት ላልኖር እችላለው። እንደሚሆን ግን አምናለው። እናንተ ግን፡ ወጣቶች ሆይ፡ አንዱ አገልጋይ ይህ ሲናገር እንደሰማችሁ አስታውሱ። ያም በመጨረሻ ይነሳልና። የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል በሚመሰረትበት ጊዜ፡ የአውሬው ምልክት እሱ ነው። የክርስቶስ ተቃዋሚ የሆነውን፡ ልጇን ትወልዳለች።

170 ሌላኛው በእግዚአብሔር ቃል የተፀነሰ ሲሆን አካሉን፡ ያለቀለት የኢየሱስ ክርስቶስን አካል ይወልዳል፡ እሷም ሙሽራይቱ ትሆናለች። የክርስቶስ አካል ገና አልተጠናቀቀም። ሰንቶቻችሁ ይህን ታውቃላችሁ? ወንድና ሴት አንድ ናቸው። ክርስቶስም አንድ አካል ነው፡ ቃሉ። ሙሽራዋ የዚህ አካል ቀሪ ክፍል መሆን አለባት። ሁለቱም፡ አንድ ላይ፡ አንድ ሥጋ ይሆናሉ። በመጀመሪያ አዳም እንደነበረ፡ ወንድና፡ ሚስቱ፡ አንድ ናቸው። አሁን፡ እሷ፡ እውነተኛዋ ሙሽራ፡ የራሷን ሀሳብ እስከማትጠቀምበት ድረስ፡ ለእርሱ በጣም የተሸጠች ናት። እርግጥ ነው፡ ሃሰቡ፡ ፈቃዱ ነው፡ ፈቃዱም ቃሉ ነው።

171 አሁን በሰው የተመረጠች ሙሽራ-የምትባለውን ተመልከቱ፡ መንፈሳዊውንም ከዛሬው ተፈጥሯዊ ጋር አወዳድሩ፡ ልክ ኤልዛቤል አክዓብን እንዳታለለችው፡ የማክስ ፋክቶር ውበት፡ ሁሉንም ነገር ትፈልጋለች። ቤተክርስቲያኒቱን ተመልከቷት፡ በተመሳሳይ መንገድ፡ በሕያው በእግዚአብሔር ቃል ጋላሞታ ናት፣ ትልቅ የሃይማኖት ተቋም፡ ትልቅ ሕንጻ፡ ብዙ ገንዘብ፡ ትልቅ ደመወዝ፡ ሁሉም ተሸጠዋል። በወንጌል ፑልፒት ላይ የቆሙ ወንዶች ምንም ችግር እንደሌለባቸው ይናገሩና፡ በዛው እንዲቀጥሉ ያደርጋሉ። ሚያታልል ብቻ፡ ያ ነው በቃ። በእርግጥም መጽሐፍ ቅዱስ እንደተናገረው፡ ዓይነ ሰውር የሆነ የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ዘመን ነው። "'ሀብታም ነኝ። ንግሥት ሆኜ እኖራለሁ። ምንም አያስፈልገኝም።' ብላለች፡" ድሀ፡ ምስኪን፡ ዕውር፡ ጎሰቋላ፡ ዕርቃን፡ እንደሆንሽ አታውቂም።" ይህ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** ካልሆነ፡ ራእይ 3፡ መቼም አንብቤ አላውቅም ማለት ነው። እሷ ናት፡ አታውቅም! አሰቡበት።

172 በጐዳና ላይ ያለ፡ ወንድ ወይም ሴት፡ ሙሉ በሙሉ እርቃናቸውን ናችሁ ብትሏቸው፡ እርቃን ናችሁ ብላችሁ ብትነግሯቸው፡ እነሱም፡ "አለ ጉዳይህ አትግባ" ይላችኋል፡ ለምን፡ የሆነ ቦታ ላይ የአዕምሮ ችግር አላቸው። በአእምሮአቸው ላይ የሆነ ችግር ተፈጥሯል።

173 ሰዎች እንዴት ማድረግ እንዳለባቸው፡ የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብ ሲችሉ፡ ዛሬ ያለን ይህን የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ሰታወሩ፡ እና፡ ሰዎች፡ ለምን፡ እናንተን እንደ እብድ ይመለከታሉ። "ዳግመኛ መወለድ አለባችሁ፡" ትላላችሁ። ዳግመኛ መወለድ አለባቸው። መጽሐፍ ቅዱስን ማመን አለባቸው።

174 እንዲህ ይላሉ፡ "ይህ ከዓመታት በፊት፡ የነበረ የአይሁድ ተረት ነው። ቤተክርስቲያናችን የራሷ መንገድ አላት" ይላሉ። ጎሰቋላ፡ አሳዛኝ፡ ዕውር፡ ራቁት፡ እና እንዲህ መሆናቸውን እንኳን አያውቁም። መ… መጽሐፍ ቅዱስም እንዲህ ዓይነት ሁኔታ እንደሚያጋጥማቸው ይናገራል።

እውነተኛ ነቢይ ይህን ማየት እንዴት ሊያመልጠው ይችላል? አላውቅም።

175 ወደ ቤተ ክርስቲያናችን ሁሉ፡ በየቦታው እየገባ ነው። በዘመናዊው አዝማሚያ ውስጥ ብቻ፡ ተመልከቱት። በራእይ ምዕራፍ 17 ላይ የተገለጸችው፡ "እርጊት ጋለሞታና ሴት ልጆቿ፡" ይህም "ለድሃው፡ ለዕውሩና፡ ለጎሰቋላው" ሕዝብ የአምላክን ቃል የሚፃረር ሃይማኖታዊ ትምህርት መስጠት ነው። "በእርሷም የባሪያዎችን፡ ከሁሉም ዘንድ—የወንዶችና የሴቶች ነፍሶችን ተገኘባት።" ሰዎችን ከመሳብ ይልቅ…

176 ክርስቶስ ቃሉን ይገልጣል፡ ይህም ሕዝቡን ይሰባል። በትላልቅ ሃይማኖቶች በትላልቅ ተግባራት በትላልቅ የቤት ዕቃዎችና በቅንጦት ነገሮች፡ የሚማረኩትን ሰዎች ወደ ቤት-ክርስቲያን አይሰብም። የእግዚአብሔር ቃል ግን የክርስቶስን ሙሽራ ይሰባል።

177 አሁን ልብ በሉ። ቤ—ቤተክርስቲያን የ—የሕዝቡን ትኩረት በሚያማምሩ አልባሳት በሚያማምሩ መዘምራን ጸጉራቸውን ባሰቆረጡት ሴቶች እና በተኳካሉ ፍቶች፡ ለ—ለመሳብ እንዴት እንደምትሞክር ማስተዋል ደስ የምል ነገር ነው። እንዴ መላእክት… ይዘምራሉ ብለው ያስባሉ። እንደ ዲያብሎስ ይዋሻሉ፡ ሌሊቱን ሙሉ ወደ ዳንስ ይሮጣሉ፡ ስለሱ ግን ምንም አያስቡ።

“ምንም ችግር የለውም። ያ ቄንጆ ነው፡” ብለው የሚያስቡት ያ ነው። ነገር ግን፡ ኢያችሁ፡ ይሁን እንጂ ይህ የተሳሳተ-ሃሳብ ነው። የእግዚአብሔር ቃል አይደለም።

178 እውነተኛው ሙሽራ ግን፡ ቃሉን በመጠበቅ፡ የእግዚአብሔርን ትኩረት ይሰባል። አሁን አስተውሉ። አሁን ክርስቶስን እናስተውል።

179 እንዲህ ትላላችሁ፡ “መልካም፡ አሁን፡ ቆይ አንድ ደቂቃ፡ ስለምትናገረው ውበትስ? ”

180 መጽሐፍ ቅዱስ፡ በኢሳይያስ 53፡2 ላይ፡ ኢየሱስ ሲመጣ፡ “እኛ እንድንወደው የሚያደርግ፡ ውበት አልነበረውም፡” ይላል። እውነት ነው? ውበት የለም። እንደ ዛሬው ሰይጣን፡ ዓለማዊ ውበት ለብሶ ቢመጣ ኖሮ፡ ሰዎች በዙሪያው ይሮጡና ዛሬ ቤተክርስቲያንን በሚቀበሉበት መንገድ ይቀበሉት ነበር። በዛሬው ጊዜ ሰይጣንን እንደሚቀበሉት ሁሉ፡ እርሱንም፡ ባመኑበትና በተቀበሉት ነበር። በእርግጠኝነት፡ ያደርጉት ነበር። ነገር ግን በእንደዚህ ዓይነት ውበት አልመጣም፡ ነገር ግን ሁሌም በባህሪው ውበት ውስጥ ይመጣል። እዚያም፡ ክርስቶስ ቄንጆ፡ ታላቅ፡ ጠንካራ፡ ብርቱ ሰው አልነበረም። እግዚአብሔር እንዲህ ዓይነቱን ሰው አይመርጥም።

181 በአንድ ወቅት አንድ ነቢይ ንጉሥን ለ—ለመምረጥ፡ ከኢሴይ ልጅ ንጉሥ ለማድረግ፡ የሌላ ንጉሥ የሳኦል ቦታ የሚወስድ፡ ለመምረጥ እንደሄደ አስታውሳለሁ። እሴይ ታላቁን፡ ትልቁን፡ ጥሩ የሚባለውን ልጁን፡ አወጣው። እንዲህም አለ፡ “አክሊሉ በራሱ ላይ ትክክል ሆኖ፡ ይታያል።”

182 ነቢዩም በላዩ ላይ ዘይቱን ለማፍሰስ ሄደ። እርሱም፡ “ጌታ አልወደደውም” አለ። እርሱም አንድ ትንሽ፡ ቍልቁል-ትከሻ ያለውን፡ ቀይ-የሚመስል ሰው ጋር እስክመጣ ድረስ፡ እያንዳንዳቸውን እምቢ አለ። ዘይቱንም በላዩ ላይ አፈሰሰው፡ እንዲህም አለ፡ “እግዚአብሔር መርጦታል።” አያችሁ? እኛ የምንመርጠው በማየት ነው። እግዚአብሔር የሚመርጠው በባህርይ ነው።

183 ባሕርይ፡ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ያለ ባሕርይ ከቶ አልተገኘም። በውስጣችሁ በመኖር እርሱን ይገልጣል። ይህ እውነት መሆኑን እናያለን። ሙሽራውን የሚስበው የእርሱ ዓለማዊ ውበት አይደለም። ኢየሱስ የሚፈልገው፡ የራሱን ባሕርይ፡ የቤተ ክርስቲያንን ባሕርይ ነው፥ ትላልቅ ሕንጻዎችን፡ ትላልቅ ሃይማኖታዊ ተቋሞችን፡ ትላልቅ አባላትን አይደለም። ሁለት ወይም ሦስት በሚሰበሰቡበት ቦታ ሁሉ እንደሚገናኝ ቃል ገብቷል። በእውነት። እውነተኛ አማኝ ተሰፋውን የሚያሳርፈው፡ የእግዚአብሔር ቃል በእውነት በሚረጋገጥበት በእዚያ ነው፡ ያ ነው። በቃሉ ይመርጣል፡ ዓለም-ወዳዶች አይችሉም። ያንን ይጠሉታል።

184 ከእሱ መፋታቷ ምንም አያስደንቅም፡ ምክንያቱም የእርሱ መገለጥ አምልጧታልና፡ የላትም። እንዴት እንደምትሆን እና እንደምታደርግ፡ ምን ያህል የዚህ ዓለም ነገር እንዳላት፡ እሱ ግድ የለውም።

185 ባህሪዋን እየፈለገ ነው፡ የክርስቶስ ባህሪ። አሁን፡ አንድ አፍታ ብቻ። ያ ነው በቃ። እርሱ ባሕሪውን የሚታንቸባርቅ ሙሽራይትን ይመርጣል፡ በዛሬው ጊዜ ያሉት ዘመናዊ አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ፡ የእርሱን መርሃ ግብር በ— በብዙ ሚሊዮን ማይልሶች ያመልጣቸዋል፡ ምክንያቱም **ይህ** እውነት መሆኑን ይክዳሉ። ታዲያ እንዴት ሊሆን ይችላል? አሁን፡ ሙሽራይቱ የምትፈጠርበትን

ቀን እየጠበቀ ነው፡ ዕብራውያን 13፥8፡ ልክ እንደነበረው፡ ልክ እንደ እርሱ። አንድ ሥጋ፡ አንድ አጥንት፡ አንድ መንፈስ፡ አንድ ዓይነት ነገር መሆን አለበት፡ በትክክል የተገነባ፡ ከዚያም ሁለቱ አንድ ይሆናሉ። ቤተክርስቲያን እንደዚያ እስካልሆነች ድረስ፡ አንድ አይደሉም። የእርሱ ባህሪ፡ የቃሉ ባህሪ፡ ለዚህ ዘመን፡ መቀረፅ አለበት። እርሷም እንደ እርሱ መቀረፅ አለባት።

186 አሁን፡ በመደምደሚያ ላይ፡ እነዚህን ነገሮች የተናገርኩበትን ምክንያት መናገር እፈልጋለሁ፡ እ—እናም እጨርሳለሁ። ባለፈው ምሽት፡ ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት አካባቢ፡ ከእንቅልፌ ነቃሁ።

187 ይህን ጥያቄ ለመመለስ ማንኛችሁንም እጠይቃለሁ። በጌታ ስም ትክክል ካልሆነ በስተቀር ሌላ ነገር ነግሬአችኋለሁ? ሁልጊዜ ትክክል ነበር። ስለዚህ እርዱኝ፡ እግዚአብሔር እውነት መሆኑን ያውቃል። በዓለም ላይ፡ በሺዎች ከሚቈጠሩ፡ የተነገሩ ነገሮች መካከል፡ በየትኛውም ቦታ አንድም ቃል ሳይፈጽም ቀርቶ አያውቅም። ሁሌም ፍጹም ሆኖ ይፈጸማል።

188 ሌላው ቀርቶ እኔ ፊኒክስ ላይ በነበርኩ ጊዜ፡ በቀደም፡ ወይም አንድ ዓመት ገደማ በፊት፡ **ወዳጆች ሆይ፡ ስንት ሰዓት ሆነ**? በ—በሚል መልዕክት ላይ ይህን ነግሬአችኋለሁ ይህን ነግሬያችሁ ነበር፡ "ሰባቱ መላእክት እዚያ እንደሚገናኙ፡" እና እነዚህ ማህተሞች እንደሚከፈቱ፡ ነግሬያችኋለሁ። በ—በዚያም **ላይፍ** መጽሔት ስለዛ ጽፏል፡ ይህ ታላቅ ነበልባል በሰላሳ ማይል ቁመት፡ በሃያ-ሰባት ማይል ስፋት፡ በአየር ላይ ይሄዳል በማለት ጽፏል። ምን እንደሆነ ማወቅ እንዳልቻሉ ተናግረዋል፡ ገና አላወቁም። እናም ዛሬ ማታ በዚህ ሕንጻ ውስጥ የተቀመጡ ሰዎች፡ ልክ እንደ ተናገረው በትክክል ሲፈጸም፡ ከእኔ ጋር ቆመው ነበር። እነዚህ ነገሮች እንደሚፈፀሙ ነግሮኝ ነበር፡ ደግሞም በትክክል ተፈጽመዋል። እነዚህ ማህተሞች እንዴት እንደተከፈቱ፡ የተሃድሶ አራማጆቹ እና የመሳሰሉት በእነዚያ ዘመናት ውስጥ የተደበቁትን ምስጢሮች እንዴት እንደተናገሩ፡ በትክክል ተናግሮኛል።

189 እንዴት፡ ሰዎች ተራራው አናት ላይ ቆመው ነበር፡ ከእነርሱ፡ ሦስት ወይም አራት አሁን እዚህ ቆመው ይገኛሉ፡ አዎ፡ ከዚያ በላይ። ወደ ኮረብታው ስንወጣ፡ መንፈስ ቅዱስ እንዲህ አለ፡ "ይህን ድንጋይ አንሣ።" እያደንን ነበር። እንዲህ አለኝ፡ "በአየር ላይ ጣለውና፡ '**የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል**' በል።" ጣልኩት። ከዚያ ትንሽ የንፋስ ሽውታ መጣ። እንዲህ አልኩ፡ "በሃያ-አራት ሰዓታት ውስጥ፡ የእግዚአብሔርን እጅ ታያላችሁ" አልኳቸው። እነዛ ሰዎች አሁን እዚህ ተቀምጠዋል።

190 በቀጣዩ ቀን፡ አሥር ሰዓት አካባቢ፡ ቆሜ፡ እንዲህ አልኳቸው፡ "ተዘጋጁ። ወደ መኪና ውስጥ ግቡ፡" ሸተራን። እኔም፡ "አንድ ነገር ሊሆን ነው" አልኩ። ትልቅ ሸለቆ ውስጥ፡ ጥርት ያለ ሰማይ ነበር። ከሰማይ የሚሽከረከር እሳት ወረደ፡ መጮህ የቻለውን ያህል ድምጽ እያሰማ፡ ግድግዳዎቹን እንደዚያ መታው። እ—እኔም ከታች ቆሜ ነበር። ባርኔጣዬን አውልቄ፡ ጭንቅላቴ ያዝኩ። ከእኔ በላይ ሦስት ጫማ ወይም አራት ጫማ ያህል መጣ፡ በዚያም ግድግዳ ዙሪያ አንድ ቦይ ቱንቢ ቈረጠና፡ ፈነዳ። ተመልሶም ወደ አየር ወጣ፡ እንደ ገናም ዞረ፡ ሦስት ጊዜም፡ ወረደ። ለሁለት መቶ ሜትሮች ያህል፡

የሜስኪት ቁጥቋጦዎችን ጫፍ እንኳን ቆርጦ ነበር። "አሜን፡" የሚሉትን ሰዎች ሰምታችኋል? ይህ በሚሆንበት ጊዜ እዚያ ነበሩ፡ አያችሁ፡ ሶስት ጊዜ ፈነዳ።

191 ከመኪኖቹ እና ከመሳሰሉት ነገሮች ሥር ሲወጡ፡ ተመልሰው በመምጣት፡ እንዲህ አሉ፡ "ይህ ቢመታህ ኖሮ፡ ምንህም አይቀርም ነበር" አሉ።

192 እኔም፡ "እ—እሱ ነው። እያወራኝ ነበር።" እግዚአብሔር በዐውሎ ነፋስ ውስጥ ተናገረ። አያችሁ? በፎቶው ላይ የምታዩት አይነት ተመሳሳይ የእሳት አምድ፡ እዚያ ቆሞ ነበር።

ወደ ላይ በወጣ ጊዜም፡ እነርሱም፡ "ይህ ምንድን ነው? " አሉኝ

እኔም፡ "በምዕራባዊው የባሕር ዳርቻ ላይ ፍርድ እየመጣ ነው" አልኳቸው።

193 ከዚያ በሁለተኛ ቀን፡ አላስካ መስመጥ ጀመረ። አያችሁ? አንዴ፡ እዚያ ፈነዳ፡ የመጀመሪያውን ምን መታ።

194 ይህን ለማሳየት፡ አንድ ነገር፡ ማድረግ አለባችሁ። አንድ ሰው ጨው በማሰሮ ውስጥ እንደጨመረ፡ ውሃ ውስጥ ጣለውና፡ እንዲህ አለ፡ "**የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል**፡ ጣፋጭ ውኃ ይሁን።" ሌላኛው ደግሞ፡ ኢየሱስም፡ ውኃ ወስዶ በወጭት ውስጥ አፈሰሰው፡ የ—የወይን ጠጅም አደረገው።

195 የሚወክለው፡ አንድ ነገር ሊኖራችሁ ይገባል። ያ ነበር፡ ወደ አየር ወጥቶ የወረደው። ይህም ትንሽ ዐውሎ ነፋስ ጀመረ። በሀያ-አራት ሰዓታት ውስጥ፡ ተራራውን በዙሪያው ያለውን ሸንተረር እስከ መቊረጥ ድረስ አናወጠ።

196 እዚህ የተቀመጠው ሬቨረንድ ሚስተር ብሌር፡ አሁን እሱን እያየሁ ነው፡ እርሱ እዚያ ነበር እና የተወሰኑትን ቁርጥራጮቹንና፡ የመሳሰሉትን አነሣ። እዚህ ላይ ቴሪ ሶዝማን፡ እነሱ፡ እዚህም ላይ የቆመው፡ እና ቢሊ ፖል ናቸው። እናም ወንድሞች፡ እዚህ ከተቀመጡት ሌሎች ብዙዎች መካከል አንዳንዶቹ፡ ይህ ሲከሰት ለማየት እዚያው ተገኝተው ነበር።

197 ይህ ልብ ወለድ አይደለም። እውነት ነው። ያ ድሮ በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን አልነበረም። አሁን ነው። አያችሁ? አምላክ እነዚህን ነገሮች ያሳየኝ ሲሆን፡ እነሱም በትክክል በትክክል እንደተባሉት፡ ተፈጽመዋል። አንድ ጊዜም እንኳ ወድቀው አያውቁም። አሁን በእሱ ላይ እመካለሁ።

198 ከጥቂት ሳምንታት በፊት፡ ራዕይ እያየው ነበር። እኔም ከ—ከፍ ባለ ቦታ ላይ ቆሜ፡ የቤተክርስቲያንን ቅድመ ዕይታ ማየት ጀመርኩ። አስተዋልኩ፡ ፊቴን ወደ ምዕራብ... ፊት፡ **በዚህ** መንገድ ቆሜ ነበር። **በዚህም** መንገድ ቈንጆ ሴቶች ተሰብስበው መጡ፡ እውነተኛ ጥሩ አለባበስ የለበሱ ነበሩ፡ ረጅም ጸጉር በቈንጆ ሁኔታ ወደ ኋላ ተስተካክሏል፡ እጅጌያቸውና፡ ቀሚሶቻቸው በጥሩ ሁኔታ የተስተካከሉ ናቸው። ሁሉም በዘመቻ ዜማ ውስጥ ነበሩ፡ ልክ፡ "የክርስቲያን ወታደሮች፡ ወደ ጦርነት እንደሚጓዙ፡ ወደ ፊት እየሄዱ፡ የኢየሱስ መስቀል ከፊት ለፊታቸው እየሄደ ነበር።" ሲያልፉም፡ ቆሜ ነበር። እናም አንድ ነገር ነበር፡ አንድ መንፈስ ነበር፡ ያም እግዚአብሔር ነበር፡ እርሱም "ይኸው ሙሽራይቱ ይህች ናት፡" አለ። እኔም ተመለከትኩና፡ ልቤ ደስተኛ ነበር። እሷም **በዚህ** መንገድ ሄደች፡ ከኋላዬ አለፈች።

199 ከአፍታ በኋላ፥ **በዚህ** መንገድ ስትመለስ፥ እንዲህ አለኝ፥ “አሁን ዘመናዊቷ ቤተክርስቲያን ወደ ቅድመ እይታ ትመጣለች” አለኝ። እነሆ የእስያ ቤተ ክርስቲያን መጣች። እኔ እንዲህ ያለ ቆሻሻ ስብስብ አይቼ አላውቅም።

200 ከተለያዩ አገራት የነበሩ፥ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት መጡ። አስከፊ ገጽታ ነበራቸው።

201 ይህን የ—የምለው በእግዚአብሔር ፊት፥ እውነቱን ለመናገር ግዴታ ስላለብኝ ነው። “የአሜሪካ ቤተክርስቲያን አሁን እየመጣች ነው፥ ቅድመ እይታ ይደረግላታል፦” ሲለኝ፥ መቼም የዲያብሎስ ስብስብ አይቼ አውቃለሁ ካልኩኝ፥ እነዚያ ነበሩ። ሴቶቹ እርቃናቸውን ነበሩ፥ ቀለሙ እንደ ዝሆን ቆዳ የመሰለ፥ ያረጀ ግራጫ-መሳይ ነገር ይዘዋል። ከፊት ለፊታቸው ይዘዉት ነበር፥ በላይኛው ክፍል ላይ ምንም አልነበራቸውም። እነርሱም እንደዚህ ዓይነት ነገሮችን እያደረጉ ነበር፥ ያ፥ እነዚህ ልጆች እዚህ የሚያደርጉት አይነት ጭፈራዎችን፥ ያ መሽከርከር እና ነገሮች፥ እንደዛ ዓይነት ሙዚቃ ይጫወቱ ነበር። ሚስ U.S.A. በመጣች ጊዜ፥ አይቻት ራሴን ልስት ተቃርቤ ነበር።

202 አሁን፥ ይህ፥ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** ነው። አገልጋዩ እንደሆንኩ ካመናችሁ፥ አሁን ታምኑኛላችሁ። በአለም ውስጥ ይህን በከንቱ አልናገርም። ይህ እውነት ካልሆነ ይህን እንድናገር የሚያደርገኝ በዓለም ሁሉ ላይ በቂ ገንዘብ የለም።

203 እሷም ስትመጣ፥ በሕይወቴ አይቼው የማላውቀው በጣም የቆሸሸ-ነገር ነበር። “አምላክ ሆይ፥ ሰባኪዎችም ሆንን ወንድሞችህ ለአንተ ሙሽራ ለማግኘት የቻልነውን ያህል ጥረት አድርገናል፥ ማድረግ የምንችለውም ይህን ብቻ ነው፦” ብዬ አሰብኩ። ልክ እንደ ሁላ ቆሚስ፥ **ይህን** ከፊት ለፊቷ ይዛ፥ ስትሽከረከር ነበር፥ የታችኛዋ ክፍል፥ ልክ **እንደዚህ፥** ከፊቷ ፊት ለፊት እንደ አንድ ነገር ይዛ፥ እነዚህ ልጆች እዚህ ባሉ በእነዚህ የዋህ ትርዒቶች ላይ እንደሚያደርጉት... እንደዚህ እየጨፈጨፈችና፥ እየዞረች ነበር። ይህች የአሜሪካ የክርስትና ነበረች።

204 በእግዚአብሔር እርዳታ፥ እርዱኝ፥ በእሱ ፊት እንዲህ ነው የሚመስለው። እ—እ... ራሴን... ልስት ጀምሬ ነበር። እንዲህም አሰብኩ፥ “ይህን ሁሉ መሞከር፥ መሰበክና፥ ማሳመንስ ለምኔ ነው? ” እያንዳንዳቸው የተቆረጠ ጸጉር ነበራቸው፥ እንዲህ እየተወዛወዙ እየዞሩ፥ **ይህን** ከፊት ይዘውት ነበር። ከዚህ ከተፈጥሮ በላይ ከሆነ ነገር ጋር ወደ ቆምኩበት፥ ዞረው መጡ። እሱን ማየት አልችልም ነበር። ሲያወራኝ መስማት እችላለሁ፥ በዙሪያዬ ነበር። ነገር ግን **በዚህ** መንገድ በዞሩ ጊዜ፥ **ይህን** ይይዛሉ። እየዞሩና እና እየሳቁ እና እየቀጠሉ ነበር፥ እንደዚያ እየቀጠሉ፥ **ይህንን** ከፊት ለፊታቸው ይይዛሉ።

205 አሁን፥ እኔ እዚያ በፊቱ ቆሜ፥ አገልጋዩ ሆኜ። “ከሞከርኳቸው ነገሮች ሁሉ፥ ያ የቻልኩት ነገር ይህ ብቻ ነው? ” “ጌታ ሆይ፥ ምን ጠቀመኝ? ምን ጠቀመኝ? ያ ሁሉ ጩኸት፥ ምልጃ፥ ማሳመን፥ ያሳየኸው ታላላቅ ምልክቶችና ድንቆችና ተአምራቶች ምን ጠቀሙኝ። እንዴት ነው እዚያ የቆምኩት፥ ለእነሱ ከሰበክኩ እና ነገሮችን ካደርኩ በኋላ ያለቀስኩት፥ ምን ጠቀመኝ? ከዚያ ሙሽራ ብዬ እንደዚህ ያለ ነገር፥ ማቅረብ አለብኝን? ”

206 እኔም በዚያ ቆሜ፡ ስመለከት፡ እሷ አለፈች። አስቡት የኋላዋ ክፍል፡ እራቁቷን ነበረች፡ **ይህንን** ከፊት ለፊቷ ይዛ፡ ልክ እንደዚህ፡ ሺሜ ጭፈራ እየተወዛወዘች፡ እግሮቿን እየወረወረች ትሄድ ነበር። እና፡ እሷ፡ ኦህ፡ ልቅ ነበረች፡ እንዴት እየሆነች እንደነበረ፡ ሰውነቷ እንደዚያ እየተንቀጠቀጠ ነበር። አሁን እ...

207 እንዲህ ትላላችሁ፡ "ይህ ምን ማለት ነው፡ ወንድም ብራንሃም?" አላውቅም። ያየሁትን ብቻ ነው የምነግራችሁ።

208 እሷም እንደዚያ ስታልፍ፡ ተመለከትኳት። ኦህ፡ ራሴን ሳትኩ። ዞርኩ። "አምላክ ሆይ፡ ተጸጽቻለሁ። አሁን ምንም—መሞከር አያስፈልገኝም። ባቆም ይሻለኛል፡" ብዬ አሰብኩ።

209 ወይዘሮ ካርል ዊልያምስ፡ እዚህ ተቀምጠሽ ከሆነ፡ ከትንሽ ጊዜ በፊት፡ የነገርሽኝ ህልም፡ ባለፈው ምሽት ያጋጠመሽ፡ ያሳሰበሽ፡ ይኸው ነው። መሪው ከእጄ ተወሰዷል።

210 ከዚያም፡ እንዲህ አሰብኩ፡ "እ—እንዲሁ ልረሳው እችላለሁ።" ሄጄ ነበር።

211 ከዚያም፡ ሁሉም በአንድ ጊዜ፡ እንደገና ሲመጣ ሰማሁ። **በዚህ** በኩል **በዚህ** መንገድ የዞረችው ያቺ ሙሽራ መጣች። እነዚህ ትናንሽ ሴቶች እንደገና ይመጣሉ፡ እያንዳንዳቸውም እንደ ስዊዘርላንድ ጀርመን፡ የመሳሰሉት፡ የመጡበትን፡ ብሔራዊ አለባበስ ለብሰው ነበር፡ እያንዳንዳቸው ያንን ዓይነት አለባበስ ለብሰው ነበር፡ ልክ እንደ መጀመሪያው፡ ሁሉም ረዥም ጸጉር ነበራቸው። እናሆ እነርሱ እየተራመዱ፡ እየመጡ ነበር። "የክርስቲያኖች ወታደሮች፡ ወደ ጦርነት እንደምሄዱ፡ ወደፊት እየዘመቱ ነበር።" ሁሉም እኛ በቆምንበት በቅድመ እይታ ቦታ በኩል ሲያልፉ፡ ሁሉም በአንድ ጊዜ፡ ሁሉም ዓይኖች በዚያ አቅጣጫ ሄዱ። ከዚያም ወደ ኋላ ዞረው፡ እየዘመቱ፡ ቀጠሉ።

212 ልክ ወደ ሰማይ መውጣት ሲጀምሩ፡ ሌላኛው ወደ ኮረብታ አፋፍ ወጣና፡ **እንዲህ** ወደ ታች ወረደ።

213 እነዚህ በቀጥታ ወደ ሰማይ መዝመት ጀመሩ። ወደ ሰልፍ ሲሄዱ፡ ከኋላ ላይ ሁለት ትናንሽ ልጃገረዶችን አስተዋልኩ፡ እንደ ስዊድን፡ ወይም ስዊዘርላንድ፡ ወይም ሌላ ቦታ ያሉ የውጭ አገር ልጃገረዶች ይመስላሉ። ዙሪያቸውን መመልከት ጀመሩ፡ እ... እኔም እንዲህ አልኳቸው፡ "ይህን አታድርጉ! ከዚያ እርምጃ አትውጡ!" እንዲህ እያልኩ ሰጮኽ፡ ራእዩ ውስጥ፡ ሆኜ ነቃው፡ እዚያ ቆሜ እጄን **እንደዛ** አድርጌ ነበር። እንዲህ ብዬ አሰብኩ፡ "መልካም... "

214 ዛሬ ማታ ያለኝን ነገር የተናገርኩት፡ ለዚህ ነው። አንድ ጥያቄ ልጠይቃችሁ እፈልጋለሁ። እኛ ከምናስበው በላይ ዘግይቷል? ቀድሞውኑ ተጠርታ እና ተመርጣ፡ ታትማ ይሁን? እንደዛ ከሆነ አንድ ተጨማሪ አይኖርም፡ ታውቃላችሁ። ይህ ሊሆን ይችላል? ኦህ፡ አዎ። ኦህ፡ አዎ።

215 በቀደም ቁርስ ላይ፡ የተናገርኩትን አስታውሱ። ወንድና ሴት በሚራቡበት የአበባ ዱቄት ውስጥ፡ አንድ ሚሊዮን ዘሮች ይወጣሉ፡ በሚሊዮን የሚቈጠሩ እንቁላሎች ይወጣሉ። ነገር ግን ከእነርሱ ብቻ አንድ ሕያው ነው፡ እና፡ ገና፡ በጣም ተመሳሳይ ናቸው፡ አንድ ከሚሊዮን ነው። እያንዳንዳቸው፡ አንድ ዓይነት

እንቊላል እና አንድ ዓይነት ዘር አላቸው። ከመካከላቸው አንዱ ይኖራል። የተቀሩት ደግሞ ይሞታሉ።

216 የትኛው የበሰለ እንቊላል እንደሆነ ማንም ሊያውቅ አይችልም፡ እና፡ ኦህ፡ ስለሱ ምንም አያውቁም። ወንድ ልጅ ይሁን ሴት ልጅ፡ አረንጓዴ ወይም ቡናማ፡ ወይም ምንም ይሁን ምን፡ እግዚአብሔር መወሰን አለበት። ውሳኔው የእግዚአብሔር ነው። የመጀመሪያው የሚገናኘው ሳይሆን፡ እግዚአብሔር መጀመሪያ የወሰነው ነው። ምናልባት፡ አንዱ **ወደዚህ** ይመጣል... አስተውላችሁ ከሆነ፡ በሙከራ መስመር ውስጥ፡ አብረው ሲመጡ ለማየት። ተመለከትኩት። እግዚአብሔር ይህን መወሰን አለበት። አንድ፡ እያንዳንዳቸው፡ አንድ ዓይነት፡ ነገር ግን በምርጫ ነው። የተፈጥሮ ልደት በምርጫ ነው። እግዚአብሔር ከአንድ ሚሊዮን ውስጥ አንዱን ይመርጣል።

217 እስራኤላውያን ግብጽን ለቀው፡ ወደ ተስፋይቱ ምድር ሲጓዙ፡ ወደ ሁለት ሚሊዮን የሚጠጉ ነበሩ። እያንዳንዳቸው በተመሳሳይ የመሰዋእት በግ ሥር ነበሩ፡ አለበለዚያ በሕይወት አይኖሩም ነበር። እያንዳንዳቸው ሙሴንና፡ ነቢዩን ያዳምጡ ነበር። እያንዳንዳቸው ለእርሱ፡ በቀይ ባሕር ውስጥ ተጠመቁ። እግዚአብሔር ጠላትን ሲያጠፋ፡ ሴቶች ከማርያም ጋር፡ ወደላይ-ወደ-ታች (በዚያን ግዜ) በባሕር ዳርቻው አጠገብ፡ ሁሉም እየጨፈሩ ነበር። ሁሉም ከሙሴ ጋር ቆመው፡ በመንፈስ ሲዘምር ሰምተውታል። እነርሱ፡ እያንዳንዳቸው፡ ከሰማይ የወረደውን መና፡ በምድረ በዳ ይመገባሉ። አዲስ መና፡ በየምሽቱ፡ ይህም የመልዕክቱ ምሳሌ ነው፡ እያንዳንዳቸው ከርሱ ይበላሉ። ግን፡ ከሁለት ሚሊዮኑ ውስጥ፡ ስንቱ ነው የተረፈው? ሁለት። ሚሊዮን ውስጥ አንድ።

218 ዛሬ ማታ በዓለም ላይ በግምት አምስት መቶ ሚሊዮን ክርስቲያኖች አሉ፡ ካቶሊኮችንም ጨምሮ። በዓለም ላይ አምስት መቶ ሚሊዮን የሚያህሉ አማኞች ነን-ባዮች አሉ። መነጠቅ ዛሬ ማታ ቢመጣ፡ ያ ማለት... ከአንድ ሚሊዮን ውስጥ አንዱ የሚቆጠር ከሆነ። እንደዚያ ነው አልልም። ነገር ግን ቢሆን ኖሮ፡ በቀጣዮቹ ሀያ-አራት ሰዓታት ውስጥ፡ አምስት መቶ ሰዎች፡ ይወሰዱ ነበር። ስለዚህ ጉዳይ ስምተህ አታውቅም። ያም ሆነ ይህ፡ ቊጥራቸው ሊታወቅ የማይችል፡ ብዙ የጠፉ ሰዎች ይኖራሉ።

219 እንግዲህ ወዳጄ፡ መጥምቁ ዮሐንስ በመጣ ጊዜ እንደሆነው፡ በእኛ ላይ፡ ሊሆን ይችላል። ደቀ መዛሙርቱም እንኳ፡ "ቅዱሳት መጻሕፍት፡ ሐ—ሐዋርያትና ነቢያት፡ ኤልያስ አስቀድሞ መጥቶ ሁሉን እንደሚያቃና የሚናገሩት ለምንድን ነው?"

220 እርሱም፡ "እላችኋለሁ ኤልያስ መጥቶአል፡ እናንተ ግን አላወቃችሁትም" አላቸው።

221 ከነዚህ ቀናት ውስጥ አንዱ እዚህ ተቀምጠን መተው እንችላለን፡ "መከራው ከመጀመሩ በፊት ስለ መነጠቅስ?"

"ቀድሞውኑ መጥቷልና አላወቃችሁትም።"

222 ሁሉም አካል፡ በአንድላይ ታትመዋል፡ ያንን አንድነት ይጠብቃሉ። በዚያ መንገድ ነው እያልኩ አይደለም። በዚያ መንገድ አይደለም ተስፋ አደርጋለሁ። ነገር ግን፡ ወዳጄ፡ እሱ ሲፈቅድ...

223 ዛሬ ማታ፡ በልባችን ውስጥ የሚሰማን ከሆነ፡ ህይወታችንና፡ የሰራናቸውን ነገሮች የሚናርም ከሆነ፡ እንደ አገልጋይ ወንድም፡ እመክርሃለሁ። ይህን ለመጀመሪያ ጊዜ በፑልፒት ላይ፡ ሊናገር ነው። በማንኛውም ጊዜ፡ በማንኛውም መንገድ፡ በሕዝብ ፊት ከተናገርኩት በላይ፡ **በዚህ** ጉዳይ ላይ፡ በዛሬው ምሽት፡ ተናግሬአለው፡ ምክንያቱም በእነዚህ ሰብሰባዎች ውስጥ ትልቅ ነጻነት ነበረኝ። የእግዚአብሔር ነቢይ እንደሆንኩ የምታምኑ ከሆነ፡ የነገርኳችሁን አዳምጡ። በልብህ ውስጥ አንድ ትንሽ ሰሜት ቢኖር፡ አሁን ወደ እግዚአብሔር ሂድ። አድርገው።

224 አንድ ደቂቃ ብቻ፡ ወንዶች። የምታገለግላቸውን የሃይማኖት መገለጫዎችን ተ—ተመልከት። ቤተክርስቲያኖችን ተመልከት። በትክክል ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ነው? ሁሉንም መሰፈርቶች አሟልተሃል? "እኔ ጥሩ ሰው ነኝ፡" በል። ኒቆዲሞስም እንደዚሁ ነበር፡ ሌሎቹም እንደዚሁ ነበሩ። ደ—ደኅና ነበሩ። አየህ? ያ ከሱ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም።

225 እና፡ ሴቶች ሆይ፡ መስታወት እንድትመለከቱና፡ እግዚአብሔር ሴት እንድታደርገው የሚፈልጋትን እንድታውቁ እፈልጋለሁ። በእግዚአብሔር መስታወት ተመልከቺ፡ አሁን በቤተክርስቲያንሽ መስታወት ሳይሆን፡ በእግዚአብሔር መስታወት ተመልከቺ፣ በሕይወትሽ ውስጥ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ መንፈሳዊ ሙሽራ ለመሆን፡ ብቁ መሆንሽንና አለመሆንሽን ተመልከቺ።

226 አገልጋዮች፡ እንደዚሁ አሰቡ። **እዚያ** ላይ የአንድን ሰው ሰሜት ለማዳን፡ ታመቻምቻላችሁ? **ይህን** ታደርጋላችሁ ካላደረጋችሁ... ከቸርች ያባሪራችኋል? እንደዚህ የሚሰማህ ከሆነ፡ ውድ ወንድሜ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም፡ አሰጠንቅቄሃለሁ፡ ከዚያ አሁኑኑ ሽሽ።

227 አንቺ፡ እመቤቴ ሆይ፡ ክርስቲያን ለመሆን የሚያስፈልጉሽን ብቃቶች ማሟላት ካልቻልሽ፡ የሰም ክርስቲያን በመሆን ሳይሆን፡ በልብሽ፡ ሕይወትሽም ልክ እንደ እግዚአብሔር የጋብቻ የምስክር ወረቀት ተቀርጾ ከሆነ፡ እዚህ ላይ፡ እንዲህ መሆን አለበት ይላልና...

228 አንተም፡ የቤተክርስቲያን አባል ሆይ፡ ቤተክርስቲያንህ እንደዚህ ካልሆነች፡ የእግዚአብሔርን ቃል ብቃት ማሟላት የማትችል ከሆነ፡ ከእርሷ ውጣና ወደ ክርስቶስ ግባ።

229 ይህ ከባድ ማሰጠንቀቂያ ነው። ይህች ከተማ፡ አንድ ቀን በዚህ ውቅያኖስ ሥር የምትዘልቅበትን ጊዜ አናውቅም፡ እናንተም አታውቁም።

230 "አንቺ፡ ቅፍርናሆም ሆይ፡" አለ ኢየሱስ፡ "አንቺ እስከ ሰማይ ከፍ ከፍ ብለሻልና፡ ወደ ሲኦልም ትወርጂያለሽ። ባንቺ የተደረገው ታምራት፡ በሶዶምና በገሞራ ተደርጐ ቢሆን ኖሮ፡ እስከ ዛሬ በኖሩ ነበር።" እነሆ ሰዶምና፡ ገሞራም በሙት ባሕር ጥልቅ ውስጥ ተኝተዋል። ቅፍርናሆምም ባሕር ውስጥ ሰምጣለች።

231 አንቺ፡ ራስሽን የመላእክት ከተማ ነኝ ብለሽ የምትጠሪ፡ ራስሽንም ወደ ሰማይ ከፍ ከፍ ያደረግሽ፡ ከተማ ሆይ፡ የፋሽንሽ እና አሸንክታቦችሽ፡ አስጸያፊ ነገሮችሽ ሁሉ፡ ሌሎች የውጭ አገራት ወደዚህ መጥተው የቆሸሸውን ነገሮቻችን እኪለቃቅሙ ድረስ፡ አንቺ እንደምታደርጊው ያደርጉ ዘንድ፡ ውብ

ወደ ሆኑት አብያተ ክርስቲያኖችሽ እና ወደ ካቴድራሎችሽ የምትልኪ፡ እነሆ፡ አንድ ቀን በባህር ግርጌ ትሰምጫለሽ፡ ታላቁ የእሳት ፈሳሽ ከበታችሽ አለ። የእግዚአብሔር ቁጣ ከአንቺ በታች እየነደደ ነው። አሸዋውንስ እስከ መቼ በዚያ ዙርያ ያኖረዋል? ከአንቺ ወዲያ ማዶ፡ አንድ ማይል ጥልቀት ያለው ውቅያኖስ፡ ተንሸራትቶ፡ ወደ ሳልቶን ባሕር፡ የወደቀለ ለታ፡ እነሆ ከፖምፔ የመጨረሻ ቀናት ይልቅ ለአንቺ የከፋ ይሆንብሻል። ንስሐ ግቢ፡ ሎስ አንጀለስ።

232 ሁላችሁም፡ ንስሐ ግቡ፡ ወደ እግዚአብሔርም ተመለሱ። የቍጣው ሰዓት በምድር ላይ ደርሷልና። ለመሸሽ ጊዜ ሳለ ሽሹ፡ ወደ ክርስቶስም ቅረቡ።

እንጸልይ።

233 የተወደድክ አምላኬ ሆይ፡ መንፈሴ፡ ሲንቀጠቀጥ፡ ልቤ የማስጠንቀቂያ እንባ እያፈሰሰ ነው። ስጠን፡ ጌታ ሆይ፡ ወንዶች እና ሴቶች የተናገርኩትን እንደ ቀልድ እንዳይቆጥሩት፡ የቤተ ክርስቲያን አባላትም ጭምር እንደ ጭፍን ጥላቻ ወይም በእነሱ ላይ ያነጣጠረ ነገር አድርገው እንዳይመለከቱት እለምንሃለሁ። ጌታ ሆይ፡ በፍቅር፡ ማየት ይሁንላቸው።

234 ሁሉን ቻይ አምላክ ሆይ፡ ቃልህን በማወጅ፡ ከዓመት ዓመት ወደ-ላይና-ታች፡ እንደሄድኩ፡ አረጋግጥልኝ። አረጋግጥልኝ፡ አምላኬ ሆይ፡ ዛሬ ማታ ቢሆን፡ እውነትን ተናግሬአለሁ። ሙሽራዋ የተገለጠላት ራእይ እውነት መሆኑን ታውቃለህ። ስምህን ተቀብያለሁ፡ ጌታ ሆይል፡ **የሰራዊት ጌታ እንዲህ ይላል** ብዬ ተናግሪያለው። ጌታ ሆይ፡ የማደርገውን እያወቅኩ እንደሆነ፡ ይሰማኛል።

235 ስለዚህ ጌታ ሆይ፡ በኢየሱስ ሰም፡ እለምንሃለሁ፡ ዛሬ ማታ፡ ሰዎች ራሳቸውን እንዲያንቀጠቅጡ፡ ኢካቦድ በደጆችና በአሕዛብ ላይ ተጽፎአልና፡ ከሚመጣውም ቍጣ እንዲሸሹ እለምንሃለው። ጥቁር ምልክት በላዩ ላይ ታይቷል። የእግዚአብሔር መንፈስ በዚህ ምክንያት ያዝናል፡ እነሱም በሚዛን ተመዝነው፡ ጎድለው ተገኝተዋል። የንጉሥ ናቡከደነፆር ድግስ እንደገና ተደገመ፡ ራሳቸውን ክርስቲያን ነን በሚሉ በከፊል-በለበሱ፡ ከሰከሩ ሴቶች ጋር ተደግሷል።

236 የሰማይ አምላክ ሆይ፡ ዛሬ ማታ እዚህ እንደሆንን፡ በኃጢአተኛ ዓለም እና በኃጢአተኛ ሰዎች ላይ ምሕረት አድርግ፡ ጌታ ሆይ። አምላኬ ሆይ፡ በጥፋት ላይ ቆሜ መለኮታዊ ምሕረትን ለመጠየቅ እየሞከርኩ ነው፡ ዛሬ ማታ ለዚህ ሕዝብ እንዲትናገርና ሙሽራህን ወደ ትኩረት እንድትጠራት፡ ጌታ ሆይ፡ በማናቸውም እምነት ምልክት ሳይሆን፡ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ድምፅ እንድትራመድ እለምንሃለው። አድረገው፡ ኦ ጌታ ሆይ። አንተ አምላክ እንደሆንክና፡ ቃልህ እውነት እንደሆነ፡ ዛሬ ማታ፡ ይታወቅ። በዚህ ሕዝብ ፊት፡ በአክብሮት፡ ለቃልህ ትኩረት እንዲሰጥ፡ እጠራሃለን።

237 ጌታ ሆይ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም፡ ስለእነሱ እጸልያለሁ። ከጥርጣሬ ጥላ ባሻገር፡ በሕዝቦቻቸው ላይ ሲትንቀሳቀ እና በልባቸው ውስጥ ያለውን ሲትነግራቸው፡ አይተውሃል። ጌታ ሆይ፡ አሁን፡ ምን እየሆነ፡ እንደሆነ፡ ታውቃለህ። አምላክ ሆይ፡ ይህ እውነት መሆኑን አንተ ታውቃለህ። በኢየሱስ ሰም፡ እለምንሃለሁ፡ መንፈስ ቅዱስ እንደገና ይማልድ፡ ጌታ ሆይ፡ ከዚህ ጉባኤ ውስጥ፡ በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ውስጥ የተጻፉትን ይለያቸው፡ ጌታ ሆይ። ስጠን፡ አምላኬ ሆይ። በሙሉ ልቤ እጸልያለሁ።

238 እነዚህ ሰዎች፡ ጌታ ሆይ፡ መልዕክቱን ለመደገፍ፡ ያላቸውን የመጨረሻ ሳንቲም፡ ይሰጡኝ። የቻሉትን ሁሉ ያድርጉ። ይሁን እንጂ፡ አምላኬ ሆይ፡ ይህን ወደ መምሰል፡ እና ወደ መቅረብ ስንመጣ ግን፡ አምላኬ ሆይ፡ ይህች ሌሊት ለእነሱ ወሮታ የምትከፍላቸውና መንፈስ ቅዱስህን በዚህ ስብሰባ ላይ የምታፈስላቸው ትሆን ዘንድ፡ እጸልያለሁ። ዛሬ ማታ፡ ፍርድ ከታች እየተንከባለለ ሲመጣ እያየን፡ የመሠዊያውን ቀንዶች አጥብቀን በመያዝ፡ ለቅሶ፡ ጩኸትና ንስሐ መግባት እንጂ፡ መዝናናትና መዝለል አይሁን። ይሁን፡ አምላክ ሆይ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ የማውቀውን ያህል በቅንነት እጸልያለሁ።

239 ወንድሜ፡ እኅቴ፡ ከዚህ—በላይ ምን ማለት እንዳለብኝ አላውቅም፡ በእናንተ ዘንድ ሞገስን ካገኘሁ፡ በእግዚአብሔር ኃይል፡ የእርሱ ነቢይ እንደሆንኩ ካመናችሁ። ይህን በአደባባይ የምናገረው ለመጀመሪያ ጊዜ ነው። ነገር ግን አንድ ዓይነት እንግዳ ማስጠንቀቂያ ይሰማኛል። ለዚህ የተጋለጥኩ አይደለሁም። እንዳልሆንኩ ታውቃላችሁ። እንደዚህ ዓይነት ድርጊት አልፈጽምም። መልእክቱን ለመናገር እና እነዚህን ነገሮች ለመናገር ፈራ ተባ ብዬ ነበር። ይህን ከመናገር ለመቆጠብ፡ ብዙ ጊዜ ዳር ዳር ብያለሁ። ነገር ግን ተነግሯል፡ ነገር ግን እውነት እንደ ተናገርኩ፡ ምስክር ሆኖ በፍርድ ቀን ይቆማል። ይህ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** ነው!... ? ...

240 ኦህ፡ ጴንጤቆስጤ፡ ለነፍስህ ሩጥ! ወደ መሠዊያው ቀንዶች ሽሽታችሁ ጩኹ፡ ከመዘግየቱ በፊት ጩኹ፡ ምክንያቱም ጩኸት ምንም ፋይዳ የማያገኝበት ጊዜ ይመጣል። ዔሳውም የብኩርና፡ ሙብቱን ሰፍራ ለማግኘት ፈልጎ፡ አላገኘውም። ካሊፎርኒያ ሆይ፡ እናንተን፡ ለጌታ አደራ እሰጣችኋለው። እናንተም፡ የፉል ጎስፔን ኮንቬንሽን ሆይ፡ የምወዳችሁ፡ ለቅቄ የወጣሁላችሁና የተጣበቅኩላችሁ፡ በሙሉ ልቤ፡ ዛሬ ማታ፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ አሳልፌ አደራ እሰጣችኋለሁ። ወደ እርሱ ሽሹ! ዲያብሎስ ከዚህ ፈጽሞ እንዲያቀዘቅዛችሁ አትፍቀዱ። እያንዳንዳችሁ፡ በመንፈስ ቅዱስ እስክትሞሉ ድረስ፡ በቃሉ ጸንታችሁ ኑሩ፡ ይህ ቃል ወደዚህ ቃል እንድትመጡ፡ ያደርጋችኋል፡ ይህ ቃል እናንተን ሴቶች እንዲያስተካክላችሁ ያደርጋችኋል፡ ይህ ቃል እናንተን ወንዶች እንዲያስተካክላችሁ ያደርጋችኋል። መንፈስ ቅዱስን አግኝቻለሁ ካላችሁና፡ ከቃሉ ጋር ካልተስማማችሁ፡ በእናንተ ውስጥ ሌላ መንፈስ አለ። የእግዚአብሔር መንፈስ በቃሉ፡ በመሲሐዊው፡ በተቀባው ቃሉ ላይ ነው። ሙሽራዋ መሲሐዊት፡ ማለትም የተቀባች ቃል መሆን አለባት።

241 በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ተነሥተን በእግራችን ዕንቍም። ዳግመኛ ድምጸን የማትሰሙ ከሆነ... ግን፡ እግዚአብሔር ቢፈቅድ፡ በጥቂት ሰዓታት ውስጥ፡ ወደ አፍሪካ እሄዳለሁ። መቼም አልመለስ ይሆናል። አላውቅም። ነገር ግን እላችኋለሁ፡ በሙሉ ልቤ፡ እውነቱን ነግሬአችኋለሁ። እግዚአብሔር እንድነግራችሁ ያዘዘኝን ነገር ሁሉ ከማወጅ ወደኋላ አላልኩም። ይህንንም በጌታ ስም ተናግሬአለሁ።

242 ይህ ወሳኝ ወቅት ነው። ይህን እንዴት መግለጽ እንዳለብኝ አላውቅም። በሦስት ወይም በአራት ጊዜያት መድረክ ለመውጣት ሞክሬያለሁ፡ ግን አልቻልኩም። ይህ ወሳኝ ሰዓት ነው። መቼም ቢሆን አትርሱት። ይህ ምናልባት፡ እግዚአብሔር የመጨረሻ ጥሪውን የሚያደርግበት፡ ጊዜ ሊሆን ይችላል።

አላውቅም። አንድ ቀን፡ የመጨረሻ ጥሪውን ያደርጋል። መቼ? አላውቅም። ነገር ግን እላችኋለሁ፡ በዚህ ራእይ መሠረት፡ ያችህ ሙሽራ ያለቀች ትመስላለች።

243 የሚመጡትን ሃይማኖቶችን ተመልከት። ተኻታ የነበረችው ድንግል ዘይት ለማግኘት ስትመጣ፡ አልተሳካላትም። ሙሽራዋ ወደ ውስጥ ገባች። ንጥቀት ሆነ። "ዘይት ሊገዙ በሄዱ ጊዜ፡ ሙሽራው መጣ።"

244 ተኻተሃል? በፍጥነት፡ ንቃ፡ ራስህን እወቅ። እያንዳንዳችን፡ በዚህች ደቂቃ፡ እንደምንሞት፡ በጌታ ስም እንጸልይ። እያንዳንዳችን፡ በራሳችን፡ መንገድ እንጸልይ።

245 ሁሉን ቻይ አምላክ ሆይ፡ ምሕረት አድርግልን። ጌታ ሆይ፡ ማረኝ። ለሁላችንንም ምሕረት አድርግልን። ምንም ነገር ብናደርግ፡ በእነዚህ ነገሮች ካልተሳካልን፡ ምን ይጠቅመናል? ኦህ ጌታ ሆይ፡ ይህች ታላቅ ከተማ በባሕር ውስጥ ከመጥለቋ በፊት እና የእግዚአብሔር ፍርዶች በዚህ የባሕር ዳርቻ ላይ ከመጥለቃቸው በፊት፡ ምሕረትን እለምናለሁ። እግዚአብሔር ሆይ፡ ሙሽራህን እንድትጠራ፡ እጸልያለሁ። አሁን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ለአንተ አደራ እሰጣቸዋለሁ። ኣሜን። ኣሜን... ? ... እውቱን ነው የነገርኳችሁ... ? ...

65-0429E የሙሽራ አመራረጥ
ቢልትሞር ሆቴል
ሎስ አንጀለስ, ካሊፎርኒያ ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2024 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

Voice Of God Recordings
P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings

P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.

www.branham.org